ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
እሁድ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 351 ነሐሴ 21 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






## ሕዝብን ከአደጋ ለማላቀቅ የውስጥ ችግራችንን መፍታት ይገባናል ሲሉ አቶ አረጋ ከበደ ገለጹ

### - የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር በዓለ ሲመት ትናንት ተካሂዷል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ሕዝብን ከአደጋ ለማላቀቅ የውስጥ ችግራችንን መፍታት ይገባናል ሲሉ አዲሱ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አረጋ ከበደ ገለጹ። የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር በዓለ ሲመት ትናንት ተካሂዷል።

ርዕሰ መስተዳድሩ አቶ አረጋ ከበደ ትናንት በበዓለ ሲመታቸው በባሕርዳር ሲካሄድ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤የክልላችንን ችግሮች በተደጋጋሚ ተነጋግረንባቸዋል። በተግባር ችግሮችን ካልፈታን ሕዝባችንን ለአደጋ እናጋልጣለን። በቁርጠኝነት ለምናደርገው እንቅስቃሴ ሁላችሁም ከጎናችን እንድትሆኑ ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

ገቢራዊ ሥራ ባለመሥራታችን ችግር ውስጥ ቆይተናልም ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በፓርቲው የጋራ ዓላማና ጥቅም በመነሳት በጋራ መሥራት ይገባል ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ።

ከዚያ ውጪ ያለው አካሄድ አዋጭ አለመሆኑንም አመልክተው፤ ከዚህ በኋላ ችግር የሚያስተናግድ አቅም የለንም። ችግሮቻችንን ካልፈታን ሀገርና ሕዝብ አደጋ ላይ

ሕዝብን ከአደጋ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## በአካዳሚው በመጪዎቹ አምስት ዓመታት የአፍሪካ ሀገራት አመራሮችን ማሰልጠን የሚያስችል ሥራዎች ይሠራሉ

ገጽ 4

## የተከሰተውን የአንበጣ መንጋ ለመከላከል የአሰሳና የኬሚካል ርጭት ሥራ እየተካሄደ ነው

ገጽ 4

## ኢትዮጵያውያን በዓለም ቻምፒዮና ማራቶን ደማቅ ታሪክ ጻፉ

ቦጋለ አበበ

በሀንጋሪ ቡዳፔስት እየተካሄደ በሚገኘው 19ኛው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ደማቅ ታሪክ ጽፈዋል።

ትናንት ማለዳ በተካሄደው የሴቶች ማራቶን ውድድር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በውድድሩ ታሪክ አንደኛና ሁለተኛ ሆነው በማጠናቀቅ አዲስ ታሪክ ሠርተዋል። በ2022 ኦሪገን ላይ በተካሄደው ቻምፒዮና የርቀቱ አሸናፊ የሆነችው አትሌት ጎተይቶም ገብረስላሴ፣ ያለምዘርፍ የኋላው፣ አማኔ በሪሶና ፀሐይ ገመቹ ኢትዮጵያን ወክለው ተፎካክረዋል።

በከፍተኛ ሙቀት ፈታኝ በነበረው ውድድር አራቱ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች አስደናቂ የቡድን ሥራ በመሥራት ለድሉ መሳካት ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። አትሌት ፀሐይ ገመቹ ለሁለት ሰዓታት በመሮጥ በቡድን ሥራው ትልቅ ሚና ከተጫወተች በኋላ አቋርጣ ወጥታለች። የእሷን መውጣት ተከትሎ ሦስቱ አትሌቶች መሪነታቸውን አጠናክረው በመቀጠል ከአንድ እስከ ሦስት

ኢትዮጵያውያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









# ስልጠናው ለሌሎች ክልሎች ተምሳሌት የሚሆን ነው

## - የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአዲስ አበባ ለሦስት ቀናት ሲሰጥ የቆየው ስልጠና ተጠናቀቀ

ማህሌት ብዙነህ


አዲስ አበባ፡- የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአዲስ አበባ ከተማ በአጀንዳ ማሰባሰብ እና ምክክር ላይ የሚሳተፉ አካላትን ለመመልመል እገዛ ለሚያደርጉ አካላት የተሰጠው ስልጠና ኮሚሽኑ እስካሁን ላልደረሰባቸው ክልሎች ተምሳሌት መሆኑን ሀገራዊ ምክክር ዋና ኮሚሽነር ገለጹ።

በአዲስ አበባ ከተማ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአጀንዳ ማሰባሰብ እና ምክክር ላይ የሚሳተፉ አካላትን ለመመልመል እገዛ ለሚያደርጉ አካላት ለተከታታይ ሦስት ቀናት ሲሰጥ የቆየው ስልጠና ትናንት ተጠናቋል።

የስልጠናውን ማጠናቀቂያ በማስመልከት የሀገራዊ ምክክር ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ እንደገለጹት፤ ስልጠናው እጅግ መሠረታዊ የሆኑ ሀገራዊ አጀንዳዎችን ለመሰብሰብ የሚያግዙ ተባባሪ አካላትን ለማፍራት ያስችላል።

የስልጠናው ዋና ዓላማ የሰለጠኑትን ተባባሪ አካላት ወደ ወረዳቸው በመመለስ ከየወረዳው የሚገኙ ባለድርሻ አካላትን በፍትሐዊ መንገድ እንዲያስመርጡ ነው። ከሚገኙት ዘጠኝ የተመረጡ ባለድርሻ አካላት ውስጥ ከእያንዳንዳቸው አስር አስር ሰው በመሆን በአጠቃላይ 90 ሰው በማስመረጥ ወደ ማእከል እንዲመጡ የሚያደርጉ ይሆናል።

ከተመረጡት 90ሰዎች በተጨማሪ ከየባለድርሻ አካላቱ ሁለት ሁለት በመምረጥ በአጠቃላይ 120 የሚጠጉ ተወካዮችን ያጠቃልላል። በቀጣይም እነዚህ ወደ ማእከል


ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ


ወይዘሮ የማርእሸት በጋሻው


አቶ ኑረዲን ረሺድ

የመጡት ተመራጮች በከተማው ከሚገኙ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተወካዮች ጋር ውይይት በማድረግ የአካባቢውና የሀገር ነው ብለው የሚያስቡትን አጀንዳ ለኮሚሽኑ የሚያቀርቡ እንደሚሆን አስታውቀዋል።

ይህም በአዲስ አበባ ከተማ የሚሰበሰብ አጀንዳ ይሆናል። አጀንዳውም የመላው ሀገሪቱ የሚሆን መልዕክትና ሃሳብ የሚገኝበት በመሆኑ በተለየ ትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል።

ስልጣናው በዋነኝነት ስለምክክር እና ውይይት ጽንሰ ሃሳብ ምንነትና ከሌሎች የግጭት መፍቻ መንገዶች የሚለዩበትን መንገድ እና ሰልጣኞች ወደ ኅብረተሰቡ በሚመለሱበት ጊዜ የኅብረተሰቡን ክፍል እኩልና አካታች በሆነ መንገድ እንዲመረጡ የሚችሉበትን መንገድ የሚያሳይ መሆኑን ኮሚሽነሩ ተናግረዋል።

በፊት የነበረው አሰራር ሰፊ ቁጥርና ጊዜ ይፈጅ የነበረ በመሆኑ የተወካዮችን ቁጥር ከ450 ወደ 90 በመቀነስ በቶሎ ለመጨረስ እና በጥር 2016 ዋናውን ምክክር ለመጀመር መታቀዱን አስታውቀዋል።

በዚህ ስልጠና ላይ ከሃይማኖት ተቋም ተሳታፊ የሆኑት አቶ ኑረዲን ረሺድ በበኩላቸው፤ ስልጠናው አሁናዊ ሀገራዊ እንቅስቃሴ ግብአት የሆነ መረጃዎችን እንዳገኙበት አስታውቀው፤ ምርጫ ሂደቱ ሁሉንም ማኅበረሰብ አሳታፊ በሆነ መንገድ የሚመረጡ ግለሰቦች ከወገንተኝነት ነጻ እና ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ ያስችላል ብለዋል።

በስልጠናው ከሴቶች ዘርፍ ተሳታፊ የሆኑት ወይዘሮ የማርእሸት በጋሻው እንደገለጹት፤ ስልጠናው ስለ ሀገራዊ ኮሚሽን ግንዛቤ እንዲኖር ከማድረግ ባለፈ ለሀገር ግንባታና አንድነት ያለውን ጥቅም በስፋት ለመረዳት ያስቻለ ነው ብለዋል።

እንዲሁም የግጭት አፈታት ዘዴዎችንና ሀገሪቱ ሰላማዊ እንድትሆን ለማስቻል ነው። በስልጠናው መሰረትም በኢትዮጵያ ስብጥሩን የጠበቀ አካታች የሆነ ሥርዓት ለመፍጠር የበኩላቸውን ድርሻ እንደሚወጡ ተናግረዋል።



## አውደ ርዕዩ የኢትዮጵያ የውሃና ኢነርጂ የቴክኖሎጂ አቅም የደረሰበትን ደረጃ ያሳያል

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- አውደ ርዕዩ የኢትዮጵያ የውሃና ኢነርጂ የቴክኖሎጂ አቅም የደረሰበትን ደረጃ ለዓለም ያሳያል ሲሉ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሁሪያ አሊ ገለጹ።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አመራርና ሠራተኞች ትናንት በሳይንስ ሙዚያም የውሃና ኢነርጂ አውደ ርዕይን ጎብኝተዋል።

በጉብኝቱ ወቅት የተገኙት ወይዘሮ ሁሪያ አሊ ፤ አውደ ርዕዩ ኢትዮጵያ ለኤሌክትሪክ ኃይልም ሆነ ለሌሎች የኢነርጂ አማራጮች የሚሆን እምቅ የውሃ ሀብትና ቴክኖሎጂ እንዳላት ያሳያል ብለዋል።

በአውደ ርዕዩ የውሃ ሀብትን በቴክኖሎጂ በመደገፍ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የሚያስችል አቅም መኖሩን ለዓለም ማሳየት ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል።

ለአንድ ሀገር ዕድገት መሠረታዊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ኢነርጂ ነው ያሉት ወይዘሮ ሁሪያ፤ የኃይል አቅርቦት ያልደረሰባቸው ገጠራማ አካባቢዎች የሶላር ሲስተምን ተጠቅሞ አቅርቦትን ለማድረስ የሚያስችል ሰፊ አቅም እንዳለ በዐውደ ርዕዩ ተመልክተናል ሲሉ ጠቁመዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የሀገርን ዕድገት ለማፋጠን እየሠራ ይገኛል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲስፋፋ በሚደረገው ጥረት ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ ሥራ እንዲከናወን ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት አካታች ቴክኖሎጂ መገንባት፣ አዳዲስ የሥራ እድል መፍጠር፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን መቀነስ እንደሚያስፈልግ ወይዘሮ ሁሪያ ገልጸዋል።

በአውደ ርዕዩ የውሃ ዘርፉን ቴክኖሎጂ ከኢነርጂ ጋር በማስተሳሰር ዓለም የደረሰበት ደረጃ መድረስ እንደምንችል አመላካች የጥናት ውጤቶችን መኅብኘታቸውን ተናግረዋል።

የኤሌክትሪክ ኃይል ከሃይድሮፓወር ብቻ ሳይሆን ከፀሐይ፣ ከነፋስና ከሌሎችም አማራጮች በሰፊው መጠቀም እንደሚቻል የተጀመሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ምስክር ናቸው፤ ይህን አቅም ማስፋት ይገባል ብለዋል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶክተር)፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶክተር) እና ሌሎችም ከፍተኛ አመራሮችና ሠራተኞች በጉብኝቱ ወቅት ተገኝተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶክተር)ና ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ አል ናህያን ለአንድ ወር የሚቆየውን የውሃና ኢነርጂ አውደ ርዕይን ነሐሴ 12 ቀን 2015 በይፋ መክፈታቸው ይታወሳል።

## ምክር ቤቱ የዋጋ ንረት እንዲረጋጋና ለዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር በትኩረት ይሠራል

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት የኑሮ ውድነት እንዲቀንስና ለሥራ አጥ ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ምክር ቤት 3ኛ ዙር 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን የመጀመሪያ የምክር ቤቱ የአስፈፃሚ አካላት የጋራ ውይይት መድረክ ትናንት አካሂዷል።

በውይይት መድረኩ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደርጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አፈጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር፤ በ2015 በጀት ዓመት በሀገሪቱ የታየው የኑሮ ውድነትና የፍጆታ ዕቃዎች የዋጋ ንረት በማኅበረሰቡ ላይ እያደረሰ ያለው ኢኮኖሚያዊ ጫና ከፍተኛ ቢሆንም በከተማ አስተዳደሩ የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋትና የሥራ አጥ ዜጎች ቁጥር ለመቀነስ የተሰሩ ሥራዎች የሚበረታቱ ናቸው። በ2016 በጀት ዓመት የገበያ ንረትን በማረጋጋት የመዲናዋን ነዋሪ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ ተጠቃሚ ለማድረግ ምክር ቤቱ ከወዲሁ ዝግጅት እያደረገ ነው ።

በ2016 በጀት ዓመት በመዲናዋ የሚታየውን የምርት፣ የፍጆታ አቃዎች የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ልዩ ልዩ ምርቶችን በብዛት እንዲገቡ በማድረግና የገበያ ትስስር የመፍጠር፣ የምርት ማከፋፈያ ማዕከላት በማስፋፋት፤ የምግብ እህሎችና መሠረታዊ የፍጆታ እቃዎች ላይ የበጀት ድጎማ በማድረግ በቅናሽ ዋጋ ለኅብረተሰቡ ተደራሽ የማድረግ ሥራ እንዲሠራ ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ሥራ እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

ከተማ አስተዳደሩ የኑሮ ውድነት ችግርን ለመቅረፍ እየሠራቸው ያለውን የከተማ ግብርናና የሌማት ትሩፋት መርሀ ግብሮች ተጠናክረው


ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር

እንዲቀጥሉ የማድረግና የማኅበረሰቡ የአትክልት፣ የፍራፍሬና እንስሳት ተዋፅኦ ምርት ፍላጎትና አቅርቦትን በማመጣጠን በትኩረት ይሰራል ብለዋል።

ያለምንም ኢኮኖሚያዊ ምክንያት የገበያ አለመረጋጋት ለመፍጠር በሚሞክሩ ማለትም የምርት እጥረት የተፈጠረ አስመስሎ በምርቶችና በፍጆታ እቃዎች ላይ የዋጋ ጭማሪ በማድረግ የኑሮ ጫና እንዲፈጠር በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ግፊት የሚያደርጉ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በአዲስ አበባ ለሥራ አጥ ዜጎች በተለያዩ ሙያ ዘርፎች የሥራ እድል እንደሚፈጠርላቸው የገለጹት አፈጉባኤዋ፤ በሚፈጠረው የሥራ እድልም የሴቶችን እኩል ተሳትፎ የሚያረጋግጥ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

ወይዘሮ ቡዜና ምክር ቤቱ በ2015 በጀት ዓመት የማኅበረሰቡን የፍትህ፣ የመልካም አስተዳደር በደልንና አገልግሎትን አሰጣጥ ችግር በመፍታት በኩል የሠራቸው ሥራዎች የሚበረታቱ መሆናቸውን አውስተው፤ በ2016 በጀት ዓመት ይህ ተግባሩን አጠናክሮ እንዲቀጥል ምክር ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል ሲሉ አመልክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በሙሰኞች ላይ እየተወሰደ ያለው ርምጃ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል!

ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ፈተና ሆነው ከሚጠቀሱ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል ሙስና ተጠቃሽ ነው። በተለይም በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ሕዝቦች ያሉባቸውን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተሻግረው ነገዎቻቸውን ብሩህ ለማድረግ በሚያደርጓቸው የእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ትልቁ ተግዳሮታቸው ሙስና እንደሆነ ብዙ ጥናቶች ያመላክታሉ።

በአንድ ሀገር ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሊከሰት የሚችለው ይህ የሙስና ችግር በቂ ትኩረት ተሰጥቶት በጥንቃቄ ሊያዝ ካልቻለ ከመልካም አስተዳደር ባለፈ መልኩ ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ የሀገርን ህልውና ስጋት ውስጥ እስከ መክተት ሊደርስ የሚችል አቅም ሊላበስ እንደሚችል ይታመናል።

ለልማት የሚውል ከፍተኛ ሀገራዊ ሀብት እንዲባክን ከማድረግ ጀምሮ፤ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዳይኖር በማድረግ ለሀገራዊ አለመረጋጋት እና ግጭት ምንጭ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ሙስና አብዛኛውን የማኅበረሰብ ክፍል በማደህየት ዜጎች ስለነጋቸው ብሩህ ተስፋ እንዲያጡ በማድረግ፤ ሀገርን ጽልመት ማልበስ የሚችል ሁለንተናዊ ጥፋት ነውና።

ሙስና እንደየሀገራቱ ተጨባጭ ሁኔታ የተለያየ መልክና መገለጫ ቢኖረውም፤ ችግሩ ዓለም አቀፋዊ ገጽታ እየተላበሰ ከመጣ ውሎ አድሯል። እንደ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ፎረም መረጃ ከሆነ ደግሞ፤ በየዓመቱ በጉቦና በስርቆት ብቻ በሚፈፀም ሙስና ከ3 ነጥብ 6 ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የዓለም ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት ይደርሳል።

ከዚህ ውስጥ 50 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ የሚሆነው ከአፍሪካ በሕገ ወጥ መንገድ የሚወጣ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ በዚህ መልኩ በሙስና የባከነ ሀብት ለመሠረተ ልማት አውታሮች፣ ለትምህርት ቤት ግንባታ፣ ለጤና ተቋማት፣ ለንፁህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት፣ በጥቅሉ ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ቢውል 43 በመቶ የሚሆኑ የዓለም ደሃ ሕዝቦች ህይወት ይቀየር እንደነበር ጥናቶች ያመላክታሉ።

ይህንን ሀገራዊ ብሎም ዓለም አቀፋዊ ችግር ለመከላከል የኢትዮጵያ መንግሥት የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። በተለይም ከለውጡ ማግስት የለውጡ አመራር ወደ ስልጣን ከመጣ ጀምሮ ችግሩን ለመቅረፍ ሰፊ ጥረቶችን አድርጓል። «ሙስና የሀገር ደኅንነት ሥጋት ሆኗል» በሚል በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሚመራ ሰባት አባላት ያሉት የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ አቋቁሞ ወደ ሥራ ገብቷል።

ቀደም ባለው ጊዜ በተለያዩ የፌዴራል መንግሥት ተቋማት በሙስና የተጠረጠሩ ባለስልጣናትንና ባለሙያዎችን ለሕግ ከማቅረብ ጀምሮ፤ ለሙስና በር የሚከፍቱ አሠራሮችን በማዘመን ችግሩን ለመከላከል የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል። ከዚህም ባለፈ ለሙስና ተጋላጭነት ያላቸውን የመንግሥት ሕግጋት፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና አሠራሮች ለማስተካከል ረጅም ርቀት ተሂዷል።

አዲስ አበባ መስተዳድርን ጨምሮ በክልል መንግሥታት አካባቢም ችግሩን ለመከላከል በተደረጉ ጥረቶች በችግሩ እጃቸው ያለባቸውን የክልል ቢሮ አመራሮች እና ባለሙያዎች ላይ ርምጃዎች ሲወሰዱ ቆይተዋል።በዚህም ችግሩ ገዝፎ የተጀመረውን ሀገራዊ የልማት እንቅስቃሴ እንዳያደበዝዘው ሰፊ ጥረት ተደርጓል።

ሰሞኑን በ2015 ዓ.ም አጠቃላይ ግምገማ ተከትሎ በሲዳማ ክልል በመልካም አስተዳደር ችግርና በሙስና የተጠረጠሩ አመራሮችን በመለየት ፣ የክልሉ መንግሥት በችግሩ ዙሪያ እጃቸው ያለበትን ከ50 በላይ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር አውሎ ምርመራ ማከናወን ጀምሯል። ይሄም እንደ ሀገር መንግሥት ችግሩን ለመከላከል እያደረገ ያለው ጥረት አንድ አካል ነው።

በክልሉ ደረጃ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም በሕዝብና በመንግሥት ሀብት ላይ የተፈጸመ ሙስና ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ሊበረታታና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባ ነው። ርምጃው በታችኛው የመንግሥት አስተዳደር እርከን ላይ ያሉ ተጠርጣሪዎችን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ምዝበራ እየተፈጸመ ዝምታን የመረጡ ኃላፊዎችን ጭምር ተጠያቂ ያደረገ መሆኑ በብዙ መልኩ ለሌሎች አስተማሪ እንደሆነ ይታመናል። ይሄው ተግባር በሁሉም አከባቢዎች እንደ ልምድ ተወስዶም ሊተገበር ይገባዋል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## በመኸሩ ወቅት የግብርናችን ፈተናዎች

ቃለአብ ዘለማይ

ከሰማኒያ በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮው በግብርና ላይ የተመሰረተ መሆኑ ይነገራል። አርሶ አደሩ በልቶ የመኖር ሕልውናውን ከማረጋገጥ አልፎ በከተሞች አካባቢ በንግድ፣ በወር ደመወዝተኝነትና በሌሎች ሥራዎች የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የመመገብ ኃላፊነትም ትከሻው ላይ ወድቋል። እንደዛሬው የበጋ ግብርና ከመታወቁና ከበሬ ጫንቃ ውጪ ሌላ አማራጮችን የመጠቀም እድል ከማግኘቱ በፊት እንኳን ሃምሳ እና ሰማኒያ ሚሊዮን ሕዝቦችን እየቀለበ አሻግሯል። ዛሬም ከመቶ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የእርሱን እጅ ይጠብቃል።

ግብርናችን ኋላቀር አሠራሮችን የሚከተል ስለነበር የምርታማነት ችግር የነበሩበት ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች ድርቅ ሲከሰት እንኳ በሌላው አካባቢ የተመረተውን ምርት ተቋድሶ የችግሩን ወቅት ለመሻገር የሚያስችል አቅም አልነበረውም። በዚህ የተነሳ በተለያየ ጊዜ ለምግብ እጥረት የተጋለጡ ወገኖቻችንን ነፍስ ለመታደግ እጃችንን ዘርግተናል፤ ከብራችንን ዝቅ አድርገን ስንዴና መሰል እርዳታዎችን ከለጋሽ ሀገራት ተመጽውተናል። ስንዴ የሚሰፍሩልን ለጋሽ ሀገራት የሚሰጡንን ድጋፍ እንደማስያዣ ተጠቅመው ለፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎታቸው ማስፈጸሚያነት እንዲያውሉት እኛው ራሳችን እድል ሰጥተናቸዋል።

በምግብ ራስን መቻል ከጥገኝነት መላቀቅ ነው፤ ከምግብ ጥገኝነት መላቀቅ ማለት ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሀገርን ክብርና ሉዓላዊነት አለማስደፈር ማለት ነው። ስለዚህ ከላይ በተገለጸው አውድ መሰረት ግብርናችን የጉሮሯችንን ችግር የሚፈታ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚያችን ፣ የክብራችን እና የሉዓላዊነታችንም ዋስትና ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በአንድ በኩል የምግብ ዋስትናችንን ለማረጋገጥ፤ እልፍ ሲልም ለውጭ ገበያ የሚተርፍ ምርት በማምረት ኢኮኖሚያችንን የመደጎም አቅጣጫ ይዞ እየሠራ ይገኛል።

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግም በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። ከነዚህም የኩታ ገጠም እርሻን ማስፋፋት፣ ምርጥ ዘር መጠቀም፣ በመስመር መዝራት፣ የአፈር ማዳበሪያ፣ ጸረ-አረምና ጸረ-ተባይ መድኃኒቶችን መጠቀም ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ የግብርና ፓኬጆች ምርታማነታችን እንዲያድግ ያደረጉና ግብርናችን ከመቶ ሚሊዮን በላይ ሕዝብን እየመገበ እንዲጓዝ ያስቻሉ አዳዲስ አቅሞቻችን ናቸው።

እንደሚታወቀው አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች የግብርና ሥራዎችን የሚያከናውኑትና ከፍተኛ ምርት የሚሰበስቡት በመኸር ወቅት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች የዓመት ጉርሳቸውን እና ስንቃቸውን የሚቋጥሩትም በአመዛኙ ከመኸሩ ወቅት በሚያገኙት በረከት ነው። ‹‹እጄን በእጄ›› እንዲሉ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን የመኸሩ ግብርናችን ራሳችን በምንፈጥረው ችግር ምክንያት ፈተናዎች እየገጠሙት ይገኛል።

የመኸሩ አዝመራ ችግር ሲገጥመው በሀገር እና በሕዝብ ላይ የሚያሳድረውን ከፍተኛ ጉዳት ካለመረዳት ወይም የግብርናውን ሥራ ሆን ብለው በማስተጓጎል መንግሥት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ እየመሰላቸው የምግብ ዋስትናችንን የምናረጋግጥበትን ወርቃማ ጊዜ የሚያውኩ አካላት ተፈጥረዋል። ባለፈው የሰሜኑ ጦርነት ሁለት የመኸር ወቅቶች ጦርነት ተደርጎባቸዋል።

ይህ በተለይም በአካባቢው አርሶ አደሮች ላይ ጥሎ ያለፈው የሞራልና የኢኮኖሚ ውድቀት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፤ በአካባቢው ያሉ አርሶ አደሮች ማምረት አለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን ለስደትና ለችግር እንዲጋለጡ ሆነዋል። ለብዙዎች ይተርፉ የነበሩት የአርሶ አደሩ እጆች ምጽዋት ለመጠየቅ ተዘርግተዋል። ዛሬም ድረስ ከገቡበት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ወጥተው የቀደመ ሕይወታቸውን ለመምራት የተቸገሩ አርሶ አደር ወገኖቻችን በርካቶች ናቸው።

በመኸሩ ወቅት አብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ዝናብ የሚያገኝ እንደመሆኑ እንደየ መልክዓ ምድሩ ፀባይ የተለያዩ አዝርዕቶች ይመረታሉ። ገበሬው በአካባቢው ካመረተው ምርት የሚተርፈውን እየሸጠ የጎደለውን እና ሌላ አካባቢ የሚመረተውን ምርት እየተለዋወጠ ሕይወትን መግፋት የኖረበት ባህሉ ነው። የጎጃም ጤፍ ፣ የአርሲ ስንዴ፣ የባሌ ገብስ ፣ የሲዳማ በቆሎ ወዘተ በተመረቱበት ቦታ ላሉ ሰዎች ብቻ የሚያገለግሉ ሳይሆን በግብይት ሥርዓት ውስጥ እያለፉ ለመላው ሕዝብ ጥቅም የሚውሉ ናቸው። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የዚህ በረከት ተቋዳሽ መሆን የሚችለው ሰብሎቹ ወቅታቸውን ጠብቀው ሲመረቱ ነው።

ቀደም ሲል የአፈር ማዳበሪያ በወቅቱ ወደ ሀገር ውስጥ አለመግባቱ ሥጋት ሆኖ እንደነበር ይታወሳል። ማዳበሪያው ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ ደግሞ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች በተገቢው መንገድ ለአርሶ አደሩ ማሰራጨት ሲገባቸው በመጋዘን ውስጥ ከዝነው የግል መጠቀሚያቸው ለማድረግ ሲሞክሩ እንደነበርም ታይቷል። እንዲህ አይነቱ ብልሹ አሠራር በምርታማነታችን ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። ማዳበሪያና አስፈላጊ የሚባሉ የግብርና ግብዓቶች በወቅቱ ተደራሽ ከማድረግ ጀምሮ በተገቢው መንገድ እስከማሰራጨት ድረስ ያለው ሂደት በጥብቅ ዲሲፕሊን መመራት እንደሚገባው ጠቁሞ ማለፍ ያስፈልጋል።

በአንዳንድ አካባቢዎች በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ምክንያት የገባውን ማዳበሪያ አርሶ አደሩ ጋር ለማድረስ አስቻይ ሁኔታዎች እንዳልነበሩም ተስተውሏል። ያም ብቻ ሳይሆን እንደምንም ብለው ቦታው የደረሱና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የወጣባቸው የአፈር ማዳበሪያዎች ነፍጥ ባነገቡ ግለሰቦች ቁጥጥር ስር ገብተው ለተለያየ ዓላማ ሲውሉ እንደነበር ታይቷል።

በተለይም በአማራ ክልል በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ምክንያት ታጣቂዎች የማዳበሪያ መጋዘኖችን እየሰበሩ ላሻቸው ሰጥተዋል፤ ላሻቸው ነስተዋል። በየወረዳው በህጋዊ መንገድ ወረፋ ይዘው ማዳበሪያ ይጠባበቁ የነበሩ አርሶ አደሮች ዛሬም ድረስ የማዳበሪያ ጥያቄያቸው በእንጥልጥል መሐል መንገድ ላይ እንደቀረ ነው። ይህም በዘንድሮው ምርታማነት ላይ የራሱን ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑን መገመት አይከብድም።

በአንዳንድ አካባቢዎች የተፈጠረው የጸጥታ ችግር አርሶ አደሩ የሥራ ጊዜውን በሚገባ እንዳይጠቀም አድርጎታል። የግብርና ሥራ የዕለት ተዕለት ክትትል የሚፈልግና ከእርሻ እስከ አውድማ ሥራ ድረስ የአርሶ አደሩን የዘወትር ትጋት የሚጠይቅ ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች የተደራጁ ቡድኖች የአርሶ አደሩን መንደሮች የጦርነት ቀጣና ስላደረጓቸው የግብርና ሥራው እየተስተጓጎለ ይገኛል።

አርሶ አደሩ እንዳያመርት ማድረጋቸው ሳያንስ ያስቀመጠውን ቀለብ ሳይቀር እያራገፉ እንዲሰጣቸው የሚያስገድዱት ነጻ አውጪ ነን ባዮች ተበራክተዋል። በተለይም የመኸሩን ወቅት እየጠበቁ የአርሶ አደሩን መንደር ማወክና የግብርና ሥራዎችን ማስተጓጎል አዲስ ፋሽን ሆኗል። ነፍጥ ያነሳሁት የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ነው የሚል እንደ ቡድን የገበሬውን የእርሻ ቦታ የጦርነት ቀጣና ባላደረገ ነበር።

ዜና

# በአካዳሚው በመጪዎቹ አምስት ዓመታት የአፍሪካ ሀገራት አመራሮችን ማሰልጠን የሚያስችል ሥራዎች ይሠራሉ

ማርቆስ በላይ

ሱሉልታ፡- የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ አቅምን በማሳደግ በመጪዎቹ አምስት ዓመታት በርካታ የአፍሪካ ሀገራት አመራሮችን ለማሰልጠን የሚያስችል ሥራዎች ይሠራሉ ሲሉ ርዕሰ አካዳሚ ዶክተር ምህረት ደበበ ገለጹ።

የአካዳሚውን የማስተር ፕላን ዲዛይን ውድድር የማጠናቀቂያና እውቅና የመስጠት መርሀ ግብር ትናንት በሱሉልታ ተካሂዷል።

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ርዕሰ አካዳሚ ዶክተር ምህረት ደበበ እንደገለጹት፤ የአካዳሚውን አቅም በማሳደግ በመጪዎቹ አምስት ዓመታት በርካታ የአፍሪካ ሀገራት አመራሮችን ለማሰልጠን የሚያስችል ሥራዎች ይሠራሉ።

የአካዳሚውን የማስተር ፕላን ንድፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ በማሰራት ከሀገር አልፎ እንደ አህጉር የአመራር ዘርፉን ለማሻሻል በርካታ ሥራዎች ይሰራሉ ያሉት ዶክተር ምህረት፤በመጪዎቹ አምስትና አስር ዓመታት ውስጥ እንደ ሀገርም ዘርፈ ብዙ የአመራርነት ሥልጠናዎችን ከመስጠት ባሻገር በግሉና በመንግሥት ዘርፍ የሚገኙ በርካታ አፍሪካ ሀገራት መሪዎች የሚሰለጥኑበት አካዳሚ እንደሚሆን ገልጸዋል።

አካዳሚው በ50 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ


ዶክተር ምህረት ደበበ

ዘመናዊና በዓይነቱ ለየት ያለ የአመራር ማሰልጠኛ መሆኑን ገልጸው፤ ደረጃቸውን የጠበቁ 300 መኝታ ክፍሎችን ጨምሮ የመመገቢያና ሥልጠና አዳራሾችና የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ስፍራዎች እንደሚገኙበት ተናግረዋል።

በአካዳሚው አመራሩን በሁለንተናዊ መንገድ ብቁ ለማድረግ ሊሠሩ ከሚገባቸው ግብዓቶችን በማሟላት ላይ ይገኛሉ። በተለይም አንጋፋ መሪዎች የሚያርፉበት፣ ላይብረሪን ጨምሮ ሙዚየምና ካምፓስ ክፍሎችን የማስፋት ሥራዎች የሚሰሩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አርክቴክት ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ሀብታሙ ጌታቸው በበኩላቸው፤ የአርክቴክት ሙያ በአገልግሎቱ የተመቸ ደህንነቱ የተረጋገጠ የሥነ ጥበብ ውጤትን የሚያበረክት የሙያ መስክ ነው።

ውድድሩ ፕሮጀክቶችን በዲዛይን በማዘጋጀት የተሻለውን በቀላሉ ለመምረጥ ያስችላል ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ ጥራት ያላቸውን ዲዛይኖች ለመለየትና አዳዲስ ሃሳብና አካሄዶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማህበር የፕሮጀክት ዲዛይን ውድድር ባህል በመሆን እንዲዳብር በመሥራት ላይ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ከተሞችን ውብ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ዲዛይኖች ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በጨረታው 14 ዓለም አቀፍ ተጫራቾች የራሳቸውን ንድፍ ያቀረቡ ሲሆን፤ በመርሀ ግብሩ የአካዳሚው የቦርድ አመራሮች ጨምሮ የአዳሚው አመራሮችና የማስተር ፕላን ድጋፍ ባለሙያዎች ተገኝተዋል።

# የተከሰተውን የአንበጣ መንጋ ስመከሳከል የአሰሳና የኬሚካል ርጭት ሥራ እየተካሄደ ነው

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የበርሀ አንበጣ በተከሰተባቸው አካባቢዎች የአሰሳና የኬሜካል ርጭት ሥራ እያካሄደ መሆኑን የምስራቅ አፍሪካ የበርሀ አንበጣ መከላከል ድርጅት አስታወቀ።

በምስራቅ አፍሪካ የበርሀ አንበጣ መከላከያ ድርጅት የመረጃና ትንበያ ከፍተኛ ባለሙያ አቶ ፈለገ ኤሊያስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ድርጅቱ ዘጠኝ ሀገራትን በአባልነት የያዘ ሲሆን፤ የአንበጣ መንጋን ድንበር የማያግደው ክስተት በመሆኑ በጋራ የመቃኘትና የመከላከል ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም ነው። በዚህ መሠረትም በኢትዮጵያ የበርሀ አንበጣ በተከሰተባቸው አካባቢዎች የአሰሳና የርጭት ሥራ እያካሄደ ነው።

አቶ ፈለገ በኢትዮጵያ ከኤርትራ በኩል የገባ አንበጣ በትግራይ፣በአማራና በአፋር ክልል መከሰቱን እና በባለፈው ሳምንት ደግሞ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሀረርጌ ምልክቶች መታየቱን ለድርጅቱ ሪፖርት እንደደረሰው ገልጸዋል።

ድርጅቱ ሀገራቶች በሚጠይቁት እርዳታ ጣልቃ ይግባ እንጂ ባለቤት ሆኖ ምንም አይነት አንበጣን የመከላከል ሥራ እንደማይሠራ የገለጹት ባለሙያው፤ በኢትዮጵያም የግብርና ሚኒስቴር ባቀረበለት ጥያቄ አንድ አውሮፕላን ኮምቦልቻ ላይ ሆኖ አሰሳ እያደረገ መሆኑንና 732 ሄክታር መሬት የኬሜካል ርጭት ማድረጉን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገራት የሆኑት ሱዳን፣ ኤርትራና ሶማሊያ አንበጣ ተከስቶባቸው እንደነበር አውስተው፤ ድርጅቱ የመከላከል ሥራ በመሥራቱ ከእነዚህ ሀገራት የአንበጣ መንጋ ወደ ኢትዮጵያ ይገባል የሚል ስጋት አለመኖሩን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ የአንበጣ መንጋ እንደሚከሰት የገለጹት አቶ ፈለገ፤ አንበጣን ሙሉ በሙሉ መከላከል ባይቻልም የመስክ አሰሳ በማድረግ ሳይስፋፋ ውስን ቦታ ላይ እያለ ማጥፋት ተመራጩ የመከላከል ዘዴ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የተከሰተውን አንበጣ እንዳይስፋፋ ለመከላከል መራቢያ ቦታቸው የሚያደርጉት የአፋር ሽለቋማ ቦታዎች ሊሆኑ እንደሚችል በመገመቱ በቀጣይ በእነዚህ አካባቢዎች ላይ የመከላከል ሥራ ይሠራል ብለዋል።

አንበጣ እንቁላል ከመጣሉ በፊት ቀለሙን ወደ ቢጫነት እንደሚቀይር ገልጸው፤ እንደነዚህ አይነት ቀለም ያላቸው አንበጣዎች የት አካባቢዎች እንዳረፉ ማኅበረሰቡ ጥቆማ እንዲሰጥና አሰሳ በማድረግ ቀድሞ የመከላከል ሥራ ይሠራል ብለዋል።

አቶ ፈለገ አሁን በኢትዮጵያ የተከሰተው አንበጣ መንጋም ከባለፈው ጊዜ ጋር ሲነፃፀር በጣም አናሳ መሆኑንና ከአቅም በላይ አለመሆኑን ገልጸው፤ ባለፉት ዓመታት ከተከሰተው የአንበጣ መንጋ እንዴት በቀላሉ መከላከል እንደሚቻል ትምህርት ተወስዷል ብለዋል።

በዚህም ከድርጅቱ በተጨማሪ ሀገሮች የራሳቸው አውሮፕላን እንዲገዙና ራሳቸውን የመከላከል አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ መደረጉን አመልክተው፤ ድጋፍ ሲጠይቁ ግን ድርጅቱ ድጋፍ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል። በአሁን ጊዜም ኢትዮጵያ አምስት የአንበጣ መከላከለያ የሚሆኑ አሮፕላኖች እንዳሏት ተናግረዋል።

# ሕዝብን ከአደጋ ለማላቀቅ የውስጥ ችግራችንን መፍታት ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንጥላለን ብለዋል።

የሀገር መከላከያ ሠራዊት ለሀገር በተለይም ለአማራ ክልል ሕዝብ እያደረገ ላለው አስተዋጽኦ እና ተጋድሎ ምሥጋና ይገባዋል ብለዋል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር በዓለ ሲመት ትናንት ሲካሄድ ለቀድሞው ርዕሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለ (ዶ/ር) እና ካቢኒያቸውም አሸኛኘት ተደርጎላቸዋል።

በበዓለ ሲመቱ ላይ የተገኙት የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሙስጠፌ ሙሐመድ አዲስ ለተሾሙት መሪዎች የእንኳን ደስ አላችሁ መልእክት አስተላልፈዋል።

በአስቸጋሪ ወቅት ክልሉን ለመሩት ለቀድሞው ርዕሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለ (ዶ/ር) ምሥጋና አቅርበዋል።

በአማራ ክልል የተፈጠረው ችግር በአጭር ጊዜ መሻሻል በማሳያቱ የተሰማቸውን ደስታም ገልጸዋል።

የአማራ ክልል ከገባበት ችግር ወጥቶ ለሀገር ምሳሌ እንደሚሆን እተማመናለሁ። የሶማሌ ክልል ከአማራ ክልል ጎን መሆኑንም ገልጸዋል።

የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሽመልስ አብዲሳ በበዓለ ሲመቱ ተገኝተው በበኩላቸው እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ፈተና ገጥሟት ያውቃል። ሁሉንም እያሸነፈች እዚህ ደርሳለች ብለዋል። አሁን የገጠማትን ፈተናም ታሸንፋለች ነው ያሉት።

በአማራ ክልል የገጠመው ችግር በሌሎች አካባቢዎች እንደሚገጥመው የገጠመ መሆኑንም ገልጸዋል።

የክልላቸው ሕዝብ በተፈለገበት ጊዜ ሁሉ ለአማራ ሕዝብ ድጋፍ እንደሚያደርግ ነው የገለጹት። የአማራ ክልል ድል ድላችን ነው ፈተናውም ፈተናችን ነው፤ ሁሉንም በጋራ እናሳካለን ብለዋል።

የተሻለችውን ኢትዮጵያ በልጆቿ መስዋዕትነት ለልጆቻችን እናስረክባለን ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ በመልዕክታቸው።

የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳድር አወል አርባ የአማራ ችግር የአፋር ችግር ነው፤ አማራ የሰውነታችን አንድ አካል ነው፤ አማራ ተረበሸ ማለት ኢትዮጵያ ተረበሸች ማለት ነው፤ ኢትዮጵያ ስትረበሽ ለጠላት በር እንከፍታለን ብለዋል።

በቤተሰብ ችግር ሲከሰት ለጠላት እጅ መስጠት ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በአንድነት ችግሮችን ማለፍ ይገባል ነው ያሉት።

የአማራ ሕዝብ ጥያቄዎች አሉት፤ ጥያቄዎችን እንዴት እንፍታ የሚለው ነው ወሳኙ ጉዳይ ብለዋል ርዕሰ መስተዳድሩ።

ለመሪዎች የመሪነት እድል መስጠት እና መሪዎችን ማገዝ ችግርን ይፈታል ነው ያሉት። የአፋር ክልል መንግሥት እና ሕዝብ ከአማራ ሕዝብና መንግሥት ጎን ነውም ብለዋል።

በበዓለ ሲመቱ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት ሌላኛው ርዕሰ መስተዳድር ደግሞ የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ደስታ ሌዳሞ ናቸው። ለአዲሱ ርዕሰ መስተዳድር እንኳን ለታላቁ ኃላፊነት አበቃዎት ብለዋል።

ኢትዮጵያ የሁላችን፤ ሕዝቦቿም የሁላችን ናቸው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ለጋራ ችግሮቻችን በጋራ መሥራት ይገባናል ነው ያሉት። የአማራ ክልል ጥያቄ ጥያቄያችን ነው፣ የጋራ ችግሮቻችንን በንግግር መፍታት ይገባናል ብለዋል።

ታላቅ ታሪክ ላለው ሕዝብ ችግሮቹን በብልኃትና በንግግር መፍታት እንደሚገባም አመላክተዋል። ከአማራ ሕዝብና መንግሥት ጎን በጋራ በመቆም ችግሮችን ለመፍታት ኃላፊነት ይዘን እንሄዳለንም ብለዋል።

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ፤ ከአባቶቻችን የወሰድነውን ጽናት ዛሬ ላይ መውሰድ ከቻልን፤ ፈጣሪን ከፈራን እና ከተከባበርን ችግሮቻችን ይፈታሉ ነው ያሉት። የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከአማራ ክልል ጎን እንደሚቆምም አረጋግጠዋል። የአማራን ሕዝብ ችግር ላልተረዱና ችግሩን ለሚያባብሱ ሰዎች ጆሮ መስጠት የለበትም ብለዋል።

በበዓለ ሲመቱ ላይ የአማራ ክልል ምክር ቤት አፈጉባኤ ፋንቱ ተስፋዬ፣ የቀድሞው የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለ (ዶ/ር)፣ የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጄኔራል ተመስገን ጥሩነህ፣ የጦር ኃይሎች ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጄኔራል አበባው ታደሰ፣ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች፣ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች መገኘታቸውን አሚኮ ዘግቧል።

# ኢትዮጵያውያን በዓለም ቻምፒዮና ማራቶን ደማቅ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለማጠናቀቅ ጥረት አድርገዋል። ውድድሩ ሊጠናቀቅ ጥቂት ሲቀረው ግን ያለምዘርፍ ከቡድን አጋሮቿ ጋር መቀጠል አልቻለችም። በዚህም በድንቅ አቋምና ጥንካሬ አማኔ በሪሶ 2:24:23 በሆነ ሰዓት የወርቅ ሜዳሊያ ስታሸንፍ የአምና ቻምፒዮኗ ጎተይቶም በ2:24:34 ሰዓት የብር ሜዳሊያ አሸናፊ ሆናለች። ኢትዮጵያውያኑን ተከትላ ሞሮኳዊቷ ፋቲማ ጋርዳዲ በ2:25:17 ሰዓት የነሐስ ሜዳሊያ አሸናፊ ሆናለች። የነሐስ ሜዳሊያውን አጥልቃ የአረንጓዴውን ጎርፍ ታሪክ ለመሥራት እስከ መጨረሻ የታገለችው ያለምዘርፍ 2:26:13 በሆነ ሰአት አምስተኛ ሆና አጠናቃለች።

ይህ ውጤት ኢትዮጵያ በቻምፒዮናው ታሪክ በሴቶች ማራቶን ትልቁ ሲሆን፤ የተመዘገበው የወርቅ ሜዳሊያም በርቀቱ ለ3ኛ ጊዜ ነው። ኢትዮጵያ በቻምፒዮናው ለመጀመሪያ ጊዜ ወርቅ ያገኘችው እኤአ 2015 የቤጂንግ ቻምፒዮና ላይ በአትሌት ማሬ ዲባባ አማካኝነት ሲሆን፤ ባለፈው ዓመት ኦሪገን ቻምፒዮናም ጎተይቶም ገብረስላሴ ለሁለተኛ ጊዜ በርቀቱ ወርቅ ማጥለቋ ይታወሳል። ጎተይቶም በትናንቱ ውድድር ያስመዘገበችው የብር ሜዳሊያም በቻምፒዮናው ታሪክ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ ሲሆን፤ አትሌቷም አምናና ዘንድሮ የወርቅና የብር ሜዳሊያ በማሸነፍ በኢትዮጵያ ደማቅ ታሪክ መጻፍ ችላለች።

የተመዘገበውን ድል ተከትሎ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የደስታ መግለጫ መልዕክት አስተላልፈዋል። “በቡዳፔስት 2023 የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በሴቶች ማራቶን ወርቅ እና ብር ላስመዘገቡ ሴት አትሌቶቻችን ያለኝን አድናቆት እገልጻለሁ። እንኳን ደስ አላችሁ። በአንድነት በመሥራት ብዙ ተጨማሪ ድንቅ ድሎችን ማሳካት እንችላለን” ብለዋል።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴም የተመዘገበውን ድል አስመልክቶ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል። ፕሬዚዳንቷ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት “ድጋሚ ደስታ! አኮራችሁን፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ደስ አለን! ይህ ነው ሕዝባችን፣ ሁላችንም የምንጋራው፣ ብቃታችሁን ያሳየ የማያሻማ ድል! ይባርካችሁ!!” ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤም “በላብ የተጻፈ ሌላ ድል እና ተጨማሪ ሜዳሊያ!፣ እንኳን ደስ አላችሁ፣ ደስ አለን!” በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። በዓለም የአትሌቲክስ ቻምፒዮና በማራቶን ያገኘነው ድል አኩሪና ጣፋጭ መሆኑን ገልጸው፤ አትሌት አማኔ በሪሶ የወርቅ፣ አትሌት ጎተይቶም ገብረስላሴ ደግሞ የብር ሜዳሊያ በማምጣት ሀገራችን በዓለም አደባባይ ደምቃ እንድትታይ፣ ሰንደቅ ዓላማችን በድል አሸብርቆ ከፍ እንዲል ማድረጋቸውን ከንቲባ አዳነች ገልጸዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ሀገራዊ ፈተና ሆኖ የቀጠለው ሕገ ወጥ ስደት ፤

ፍልሰት እንበለው ስደት ሰፊና ውስብስብ የሰው ልጆች ታሪክ ነው። በብዙ ሺዎች የሚቆጠር ዓመታትን ያስቆጠረ ሰብዓዊ ክስተትም ነው። ሰዎች ከቅድመ ታሪክ አንስቶ በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች ማለትም በአየር ንብረት ለውጥ፣ በሕዝብ ብዛት፣ በኢኮኖሚያዊ ዕድሎች፣ በፖለቲካዊ አለመረጋጋት፣ በባህላዊና ማህበራዊ ተጽዕኖዎች የተነሳ ከቦታ ወደ ቦታ ይፈልሳሉ፣ ከሀገር ወደ ሀገር ይሰደዳሉ።

በአምላክነት ምኞት ወይም ጥንተ ዓብሶ /Original sin/ የተነሳ አደም ኃጢያተኛ ሆኖ ልጅነቱን አጥቶ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ጸብ ተጣልቶና መርገም መጥቶበት ከገነት ከተባረረበት ከዛ ሩቅ ዘመን አንስቶ ዘረ አዳም ፍልሰተኛና ስደተኛ ነው። ሳይንሱ ደግሞ የሰው ዘር ወይም ሆሞ ሳፒንስ ከአፍሪካ ተነስቶ ወደ ሌሎች አህጉራት እንደተስፋፋ ይነግረናል። የዕለት ጉርሱን ለማግኘት፣ በአየር ንብረት ለውጥ የተነሳና አዳዲስ አካባቢዎችን ከማግኘትና ከማወቅ ጉጉቱ የተነሳ እግሩ በመራው ሲሰደድ ኖሯል።

በጥንታዊው የታሪክ ሂደት በስልጣኔዎች መካከል ሳይቀር ስደት መከሰቱን የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ። ሜሶፖታሚያንስ፣ ግብጻውያን፣ ግሪኮችና ሮማንስ በግዛታቸው ውስጥም ሆነ ውጭ በጦርነት፣ በንግድ፣ በቅኝ ግዛትና ሀብት ለመፈለግ ሲሉ ይሰደዱ ነበር። በመካከለኛው ዘመን ደግሞ በሮማን ግዛት ወይም ኢምፓየር መንኮታኮት የተነሳ፣ በቪኪንግ መስፋፋት፣ በሞንጎሎች ወረራና በመስቀል ጦርነቶች የተነሳ ሕዝብ በስፋት ተሰዷል።

ከ15ኛው መክዘ እስከ 18ኛው መክዘ የነበረው የአሰሳ ዘመን በሰው ልጆች ታሪክ አሻራውን ትቶ ያለፈ ከፍተኛ ስደት ተከናውኗል። አውሮፓውያኑ ክርስቶፈር ኮለምበስ፣ ቫስኮ ዳ ጋማና ፈርዲናንድ ማጅላን አዳዲስ የንግድ መስመሮችንና ስፍራዎችን ለማሰስ ባደረጉት ጉዞ አሜሪካን፣ አፍሪካን፣ እስያንና የሰላማዊ ውቅያኖስ ደሴቶችን በማግኘታቸው በአውሮፓውያን ቅኝ እንዲገዙ ፈር ቀድዷል። ይሄን ተከትሎ በተስፋፋው የባሪያ ንግድ ደግሞ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ አፍሪካውያን ከቀዬአቸው ተፈንግለው ወደ ሰሜንና ደቡብ አሜሪካ ተግዘዋል።

በ19ኛውና በ20ኛው መክዘ ደግሞ በኢንዱስትሪው አብዮት፣ በፖለቲካዊ አለመረጋጋት በተሻለ ኑሮ ፍለጋ የሰው ልጅ በገፍ ተሰዷል። የአይርላንድ የድንች ርሀብ፣ የካሊፎርኒያ የወርቅ ፍለጋና የኢንዱስትሪ አብዮቱ ታላቅ የሕዝብ ስደትን አስከትለዋል። በዚህም የአይሪሽና የጂዊሽ ዲያስፓራዎች ተፈጥረዋል። ሁለቱ የዓለም ጦርነቶችም ከፍተኛ የሕዝብ ስደት ቀስቅሰዋል። በአፍሪካና በእስያ ቅኝ ግዛት ከተንኮታኮተ፣ ሶቭየት ሕብረት ከፈራረሰች በኋላና ሉዓላዊነትን ተከትሎ ከፍተኛ የሕዝብ ስደትና ፍልሰት ተከስቷል።

ኢትዮጵያውያንም ይህን የሰው ልጅ ታሪክ በራሳቸው አውድ ተጋርተውታል። የሰሜኑ ወደ ደቡብ፣ የደቡቡ ወደ ሰሜን ፤ የምዕራቡ ወደ ምስራቅ፣ የምስራቁ ወደ ምዕራቡ የሀገራችን ክፍል ፈልሷል። ቀይና ነጭ ጤፍ ሲቀላቀል ለመለየት እንደሚቸግረው ኢትዮጵያውያን በጋብቻ፣ በሃይማኖት፣ የሀገር ሉዓላዊነትን ለማስከበር በተደረገ ተጋድሎ፣ ወዘተረፈ እርስ በርስ በአጥንትና በደም ተጋምደዋል። ምንም እንኳ ጽንፈ በረገጠ ጽንፈኝነት እየተፈተኑ ቢሆንም።

በተለይ ባለፉት 50ና ከዚያ በላይ አመታት መንገድና መጓጓዣ በመስፋፋቱና በመዘመኑ፤ የሀገሪቱ ፖለቲካም መጠፋፋት ላይ መጎንቆሉ፤ የተሻለ ኑሮና ኢኮኖሚያዊ ዕድል የሚሻው ትውልድ እየተበራከተ መምጣቱ፤ በሀገራችን የተንሰራፋው ሥራ አጥነትና ድህነት፣ ሀገራዊ አለመረጋጋት፣ የገነገነ ሙስና፣ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ፣ ድርቅና ርሀብ በሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ታግዞ በተለይ ሕገ ወጥ ስደቱ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። ዜጎች በሀገራቸው ሰርተውና ጥረው ግረው ከመለወጥ ይልቅ ስደትን መምረጣቸው ለተለያዩ ችግሮች እያጋለጣቸው ነው። የሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎችንና ደላላዎችን የማይጨበጥና ሀሰተኛ ማማለያ እየሰሙ የባሕር፣ የበርሀ፣ የአውሬ፣ የአሸባሪና የአረመኔ የድንበር ጠባቂ ሰለባ እያደረጋቸው ይገኛል።

ለአካላታቸው ማለትም ለኩላሊትና ጉበታቸው ሲባል በሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች እየተገደሉ፤ አካላቸው እየጎደለ ነው። ሴቶች አልፎ አልፎም ወንዶች ሳይቀሩ እየተደፈሩ፤ ኀልቆ መሳፍርት የሌለው ግፍ፣ ሰቆቃና ስቃይ እየተፈጸመባቸው ይገኛል። ይሄን ሁሉ ፈተና አልፈው ሳውዲ፣ ባህሬን፣ ኩየት፣ ዩናይትድ ኤሚሬት፣ ሶሪያና ሊባኖስ ከደረሱ በኋላ በሕገ ወጥ መንገድ ስለሚቀጠሩ ሌት ተቀን የሰሩበት የደላላና የአሰሪ ሲሳይ ሆኖ ይቀራል። በዚህ ብስጭት ለአእምሮ ሕመም ይዳረጋሉ። በአሰሪዎቻቸው አሰቃቂ ግፍና በደል ይፈጸምባቸዋል። እንደ ደቡብ አፍሪካ ባሉ ሀገራትም ሰርተው በበሉ በተለወጡ በሀገሬው ይገደላሉ። ይዘርፋሉ።

በሕገ ወጥ መንገድ በሱዳን፣ በሞያሌና በጅቡቲ የሚወጡ ዜጎች መንገድ ላይ በውሃ ጥም፣ በርሀብ፣ በአውሬ፣ በሰው አካላት Human organs ነጋዴዎች እየተገደሉና እየሞቱ፣ ባሕር ላይ የአሳ ነባሪ ሲሳይ እየሆኑ፣ በሊቢያና በየመን በአጋቾች እየተሰቃዩ፣ በድንበር ጠባቂዎች በግፍ በጥይት እየተደበደቡ እንደሚገደሉ እያዩና እየሰሙ፤ ሕገ ወጥ ስደተኞች ግን ከዓይናቸውና ከጆሯቸው ይልቅ አዘዋዋሪዎችንና ደላላዎችን ማመን በመምረጣቸው ዛሬም ለማየት የሚዘገንን ለመስማት የሚሰቀጥጥ ሰቆቃ እየተፈጸመባቸው ይገኛል።

ሕገ ወጥ እየተባሉ በአረብ ሀገራት ማጎሪያዎች እየተሰቃዩ ነው። ኢትዮጵያ ነብዩ መሐመድ የሚወዷት፣ መልካም ምድር፣ የታማኞችና የደጎች፣ ፍትሕ የሚያውቁ ሕዝቦች ሀገር እንደኾነች የተናገሩላት፣ አምነው መልእክተኞችን የላኩባት፣ እርሷን አትንኳት ያሉባት የቃል ኪዳን ሀገር ብትሆንም ሳውዲ አረቢያ በዜጎቻችን ላይ የምትፈጽመው ኀልቆ መሳፍርት የሌለው ግፍ ግን ከዚህ ፍጹም የሚቃረን ነው፡፡

በተለይ በሳውዲ አረቢያ ዜጎቻችን በተለየ መንገድ በደልና ስቃይ ይፈጸምባቸዋል። ዓለም አቀፉ የስደተኞች ማህበር እንዳስታወቀው የሳዑዲ አረቢያ መንግሥት ከኅዳር 2009 ዓ.ም አንስቶ ስደተኞችን በግዳጅ ወደ ሀገራቸው መመለስ ከመጀመሩ በፊት በሀገሪቱ 500 ሺህ የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን ይኖሩ ነበር። በዚህም ከግንቦት 2009 እስከ መጋቢት 2011 ዓ.ም ባለው ጊዜ 260 ሺህ የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን በአማካይ በየወሩ 10 ሺህ ሰዎች በግዳጅ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ተደርገዋል።

ዓለም አቀፉ የስደተኞች ማህበር እንዳስታወቀው በግዳጅ ወደ ሀገራቸው የመመለሱ ሂደት አሁንም ቀጥሏል። የሳዑዲ አረቢያ የሀገር ውስጥ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው ከተለያየ ዓለም በመምጣት በሳዑዲ እየኖሩ ሕግ የጣሱ 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሰዎች በፖሊስ ታስረዋል። ከነዚህ ውስጥ 51 በመቶ የሚጠጉት ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ በአጠቃላይ 895 ሺህ የሚጠጉት ኢትዮጵያውያን ደግሞ በግዳጅ ወደ ሀገራቸው የሚመለሱ መሆናቸውን ሪፖርቱ አመላክቷል። ሰሞኑን ደግሞ ሒውማን ራይትስ ዋች ባወጣው ሰፊ ሪፖርት ኢትዮጵያውያን በሳውዲ ድንበር ጠባቂዎች በግፍ እንደተገደሉ፤ ከፍ ሲልም በሰብዓዊ ፍጡር ላይ የሚፈጸም ወንጀል እንደሆነ እየተዘገበ ይገኛል።

የሳውዲ ድንበር ጠባቂዎች ከመጋቢት 2022 እስከ ሰኔ 2023 ባለው ጊዜ ውስጥ የየመን-ሳውዲን ድንበር ለመሻገር በሞከሩት በትንሹ በመቶዎች የሚቆጠሩ ስደተኞችንና ጥገኝነት ፈላጊ ኢትዮጵያውያንን ገድለዋል። የሳውዲ ባለሥልጣናትም በአንድ በኩል የራሳቸውን ገፅታ ለመገንባት በስፖርታዊ ውድድር ላይ በቢሊዮኖች ወጪ ሲያደርጉ በሌላ መልኩ ደግሞ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሴቶችና ሕፃናትን ከቀረው ዓለም እይታ በተሰወረ መንገድ ይገድላሉ። ሳውዲ አረቢያ በስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ላይ የምትከተለውን ገዳይ ፖሊሲ ጊዜ ሳትሰጥ በአስቸኳይ መሻር አለባት። ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሀገሮች በበኩላቸው ተጠያቂነት እንዲኖር ግፊት ማድረግ ያለባቸው ሲሆን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም በጉዳዩ ዙሪያ ምርመራ ማካሄድ አለበት ሲል ሒውማን ራይትስ ዎች ያሳስባል።

ሒዩማን ራይትስ ዎች ዛሬ ያወጣው ሪፖርት፣ የሳውዲ ድንበር ጠባቂዎች ከመጋቢት 2022 እስከ ሰኔ 2023 ባለው ጊዜ ውስጥ የየመን–ሳዑዲን ድንበር ለመሻገር የሞከሩትን በትንሹ በመቶዎች የሚቆጠሩ ስደተኞችንና ጥገኝነት ፈላጊ ኢትዮጵያውያንን ገድለዋል። ስደተኞችን የመግደል ርምጃ የሳውዲ አረቢያ መንግሥት ፖሊሲ አካል ሆኖ ከተፈፀመ፣ እነዚህ ግድያዎች ቀጣይነት ያላቸውና በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ይሆናሉ ይላል።

ባለ 73 ገጹ የሒውማን ራይትስ ዎች ሪፖርት ሰሞኑን ይፋ እንዳደረገውና ዓለም አቀፍ ብዙኃን መገናኛዎችም እንደተቀባበሉት፤ ተኩስ በእኛ ላይ እንደ ዝናብ አወረዱብን ሲሉ ስደተኞች ይናገራሉ። የሳውዲ ድንበር ጠባቂዎች ብዙ ስደተኞችን ለመግደል ፈንጂ እንደተጠቀሙ፤ በስደተኞች ላይ በቅርብ ርቀት ሆነው እንደተኮሱባቸው እና ብዙ ሴቶችንና ሕጻናትን ጨምሮ፣ ሰፊ እና ስልታዊ በሆኑ ጥቃቶች መግደላቸውን አረጋግጧል። በአንዳንድ አጋጣሚዎች፣ የሳዑዲ ጠረፍ ጠባቂዎች ስደተኞቹን በየትኛው አካላቸው ላይ እንደሚተኩሱባቸው እየጠየቁ በቅርብ ርቀት ተኩሰው ገለዋቸዋል።

በተጨማሪም እነዚህ የሳውዲ ድንበር ጠባቂዎች ወደ የመን ለመመለስ የሞከሩ ስደተኞች ላይም ፈንጂ እንደተኮሱባቸው ከጥቃቱ የተረፉ ስደተኞች ለተቋሙ ገልጸዋል። በሒዩማን ራይትስ ዎች ድርጅት የስደተኞችና ፍልሰተኞች መብቶች ተመራማሪ የሆኑት ናዲያ ሃርድማን እንደሚሉት” የሳዑዲ ባለሥልጣናት በነዚህ ሩቅ በሆኑ ድንበር አካባቢዎች ከቀረው ዓለም እይታ በተሰወረ መልኩ በመቶዎች የሚቆጠሩ ስደተኞችና ጥገኝነት ፈላጊዎችን ይገድላሉ። የሳውዲን ገፅታ ለመገንባት ለጎልፍ ፕሮፌሽናል፣ ለእግር ኳስ ክለብ እና ለዋና ዋና መዝናኛ ዝግጅቶች ግዥ በቢሊዮኖች የሚቆጠር ሀብት ወጪ ማድረጋቸው በእነዚህ ዘግናኝ ወንጀሎች ላይ ያለውን ትኩረት ማዛባት የለበትም። “

ሒውማን ራይትስ ዎች ከመጋቢት 2022 እስከ ሰኔ 2023 ባለው ጊዜ ውስጥ የየመን-ሳዑዲን ድንበር ለመሻገር የሞከሩትን 38 ኢትዮጵያውያን ስደተኞችና ጥገኝነት ፈላጊዎችንና 4 ዘመድና ጓደኞቻቸውን ጨምሮ ለ42 ሰዎች ቃለ መጠይቅ አድርጓል። የሒውማን ራይትስ ዎች ማህበራዊ ድረ-ገፆች ላይ የተለጠፉ፣ ከሌሎች ምንጮች የተገኙና በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ስኩዌር ኪሎ ሜትሮችን ካካለሉ የሳተላይት ምስሎች የተገኙ ከ350 በላይ ቪዲዮዎችን እና ፎቶግራፎችን መርምሯል።

በግምት 750,000 ኢትዮጵያውያን በሳውዲ አረቢያ ውስጥ እየሠሩ ይኖራሉ። ብዙ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ቢኖሩአቸውም በቅርቡ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል እንደነበረው በጦር መሣሪያ የታገዘ አሰቃቂ ግጭት፣ አብዛኞዎቹ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደርስባቸው ሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት ሀገራቸውን ጥለው ይሰደዳሉ። ሒዩማን ራይትስ ዎች በየመንና ሳውድ ድንበር አካባቢ የተፈፀሙ የስደተኞችን ግድያ ከ2014 ጀምሮ በሰነድ ያዘጋጀ ሲሆን፣ ግድያዎቹም ሆን ተብለው የተፈፀሙና የሟቾችም ቁጥር የበዛና የአገዳደላቸው ሁኔታም የከፋ ነው።

ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች በባህር ላይ ለመጓዝ ምቹ ባልሆኑ መርከቦች የኤደንን ባህረ–ሰላጤ እንዳቋረጡ ተናግረዋል። ከዚያም የየመን ሕገ ወጥ ሰው አዘዋዋሪዎች በሳውዲ ድንበር በሁቲ ታጣቂ ቡድን ቁጥጥር ሥር ወደሚገኘው ሰዓዳ ግዛት ወስደዋቸዋል። ብዙዎች የሁቲ ኃይሎች ከሕገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች ጋር እንደሚሠሩና እንደሚዘርፏቸው ወይም ስደተኞችን ወደ ማቆያ ማዕከላት እንደሚያስተላልፉ እና ሰዎች “የመውጫ ክፍያ” እስኪከፍሉ ድረስ በዚያ እንግልት ይደርስባቸዋል ብለዋል።

እስከ 200 የሚደርሱ ስደተኞች በቡድን ሆነው ወደ ሳውዲ አረቢያ ድንበር ለመሻገር በየጊዜው ይሞክራሉ። ብዙ ጊዜ የሳውዲ ድንበር ጠባቂዎች ወደ ኋላ ከገፏቸው በኋላ ብዙ ሙከራ ያደርጋሉ። ስደተኞች ቡድኖቻቸው ከወንዶች የበለጠ ሴቶች እንደሚበዙ ተናግረዋል። ሒውማን ራይትስ ዎች ከእነዚህ መረጃዎች ጋር የሚጣጣሙ የሳውዲ ድንበር ጥበቃ ቦታዎችን ከሳተላይት ምስሎች ለይቷል። በተጨማሪም ሒውማን ራይትስ ዎች ከጥቅምት 11/2021 እስከ ጥር 1/2023 በአንዱ የሳውዲ የድንበር ጥበቃ ጣቢያ አካባቢ ከደፈጣ የተጠበቀና ፈንጂን መቋቋም የሚችል የሚመስል ተሽከርካሪ መታየቱን ለይቷል።

ተሽከርካሪው በጣራው ላይ የተገጠመ ከባድ መትረየስ ያለው ይመስላል። ከሳውዲ ድንበር ጠባቂዎች አቅጣጫ በሞርታር ፕሮጄክታይሎች እና በሌሎች ፈንጂ መሳሪያዎች ድንበሩን እንዳቋረጡ ጥቃት እንደደረሰባቸው በቡድን የሚጓዙት ሰዎች ገልጸዋል። የሳውዲ ድንበር ጠባቂዎች ፈንጂ መሳሪያዎችን ስለመጠቀማቸው ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ሰዎች 28 ክስተቶችን በመግለፅ አስረድተዋል። በሕይወት የተረፉ ሰዎችም ሳውዲዎች አንዳንድ ጊዜ በማቆያ ቦታዎች እንደሚያግቷቸውና ለወራት እንደሚያቆዩአቸው ገልጸዋል።

ሳውዲ አረቢያ በስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ላይ በፈንጂና በቅርብ ርቀት በመተኮስ ማጥቃትን ጨምሮ ገዳይ ኃይልን ለመጠቀም የተቀመጠ ማንኛውንም ፖሊሲ በአስቸኳይ መሻር አለበት። መንግሥት በየመን ድንበር ላይ ሕገወጥ ግድያ፣ ማቁሰል እና ሰቆቃ የሚፈፅሙትን የደህንነት አባላትን መርምሮ በተገቢው መቅጣት ወይም መክሰስ ይገባል። ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግሥታት ሳውዲ አረቢያ የዚህን አይነት ገዳይ ፖሊሲ እንድታቆምና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ግፊት ማድረግ አለባቸው።

ከዚህ ጋር በተገናኘ የሚመለከታቸው መንግሥታት በድንበር ላይ እየተፈጸሙ ያሉ ጥሰቶች ላይ ታማኝ በሆነ መልኩ በሳዑዲ እና የሁቲ ባለስልጣናት ላይ ማዕቀብ መጣል አለባቸው። በተባበሩት መንግሥታት የሚደገፍ ምርመራ በማቋቋም በስደተኞች ላይ የሚደርሰው በደል ግድያዎችም በሰብዓዊነት ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ስለመሆናቸው መመርመር አለበት። ሃርድማን “የሳውዲ ድንበር ጠባቂዎች ባልታጠቁ ሰላማዊ ዜጎች ላይ እንደሚተኩሱ ያውቃሉ ወይም ማወቅ ነበረባቸው” ብላለች። “በኢትዮጵያውያን ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ላይ ለሚፈፀሙ ወንጀሎች ፍትህ ካልተገኘ ተጨማሪ ግድያዎችንና እንግልቶችን ያባብሳል። “ስትል ታስጠነቅቃለች።

ሻሎም ለሀገረ ኢትዮጵያ !

አሜን ።

# 28 ዓመታትን በአስከሬን መርማሪነት

**እፀገነት አክሊሉ**

የሰው ልጅ ሕይወት በሁለት ጫፎች መሃል ነው፡፡ በውልደትና በሞት መሃል፡፡ ሰው የተወለደ ዕለት ደስታው እጥፍ ድርብ ነው፡፡ ያንን ደስታ ለማክበርም እናት አባት ቤተሰብ ዘመድ አዝማድ ሁሉ የሚችለውን ያደርጋል፡፡ ኋላም የተወለደው አድጎ ተምሮ ቁም ነገር ይደርስ ዘንድም ምኞቱም ሆነ የሚደረገው ነገር ይቀጥላል፡፡

ይህ ሰው ግን ዞሮ ዞሮ በምድር ላይ እንዲኖር የተፈቀደለት ጊዜ መጠን አለውና ያ ቀን ሲደርስ ደግሞ ወደ ፈጣሪው ይጠራል፡፡ በዚህ ጥሪ ጊዜም አሸኛኘቱ እንደባህል እንደ እምነቱ ብዙ ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ግን ይህ ሰው የሞቱ ዕለት እንደ ውልደቱ ሰዎች ተሰብስበው ሊያዩት አይችሉም ቢፈልጉ እንኳን ፍርሃት ሀዘን አለና ማንም በቀላሉ አይቀርበውም፡፡

ታዲያ በአንድ ወቅት ሰው የተባለው ይህ አካል ቀኑ ሲደርስ ደግሞ ስያሜው ይቀየርና "አስከሬን" ይባላል፡፡ አስከሬንን ደግሞ ማን ይነካዋል፤ ማንስ ይጠጋዋል፤ እንኳን አስከሬኑን የሚሸኝበትን ሳጥን ብዙዎች በሩቁ እንሸሸዋለን፡፡

ነጋሽ አበራ ግን ከብዙዎቻችን ለየት ያለ ሙያ ያለው ሰው ነው፡፡ ይህንን ሰው የሚፈራውን ስሙን መስማት ራሱ የሚያባንነውን አስከሬን መመርመር እንጀራው ነው፡፡ ነጋሽ አስከሬንን ከማየት አልፎ ተርፎ አጋልበጦ ውስጥ አካሉ ድረስ ዘልቆ ገብቶ ምን ሆኖ ሞተ የሚለውን የሚያጣራ ባለሙያም ነው፡፡

ተወልዶ ያደገው ኮሪያ ሰፈር ነው፡፡ ለቤተሰቦቹ ሶስተኛ ልጅ ሲሆን እድሜው ለትምህርት ሲደርስም የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን የጀመረው ሕብረት ፍሬ በሚባለው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ወቅቱ የወታደራዊው አገዛዝ ደርግ ዘመነ መንግሥት በመሆኑና እሱም የወታደር ልጅ ነበርና የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በቀጥታ ወደ ውትድርና ገባ፡፡ በወታደር ቤትም እስከዛሬ ድረስ የሚጠቀምባቸውን የሕይወት ተሞክሮዎች ቀስሞ ለእናት ሀገሩ ዘብ ሆኖ ከቆየ በኋላ የመንግሥት ለውጥ ሲመጣ ተቀናሽ በመሆን ወደ ቤተሰቡ ይመለሳል፡፡

ነጋሽ እንደሚለው ቤተሰቦቹ በኢኮኖሚ ደከም ያሉ በመሆናቸውና ብዙ ልጆችም ስላሏቸው ገና በልጅነት እድሜው ነበር ራስን ማስተዳደር የውዴታ ግዴታ የሆነበት፡፡ በ120 ብር የወር ደመወዝ ወታደር ሆኖ ለእናት ሀገሩ ከመዝመቱም በላይ በሚያገኘው ገንዘብም ራሱንና ቤተሰቡን ያግዝ ነበር፡፡

በ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ ወደ ቤተሰቦቹ በመመለስ ያቋረጠውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በመድኃኒዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለመቀጠሉም ይናገራል፡፡

".....ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰብ ልጅ በመሆኔና የወታደር ልጅም ስለሆንኩ ገና ከፍ እንዳልኩ ነው ወታደርነትን የመረጥኩት፤ ወታደር ቤት ያለው ሕይወትም ችግርንም ደስታንም መሰናክልንም ብቻ የሕይወት አጋጣሚዎችን ሁሉ እንዴት ማለፍ እንዳለብኝ አስተምሮኛል ጠንካራ ሰውም አድርጎኛል" ይላል፡፡

በወቅቱ ለትምህርት ትኩረት ይሰጥ እንዳልነበር የሚናገረው ነጋሽ ቤተሰብም የእለት ጉርስን አግኝቶ ስለማደር እንጂ ስለትምህርት ያን ያህል እውቀቱም አላልነበራቸውም፡፡ ልጆችንም ተማሩ በማለቱ በኩል የሚጠቀስ ተግባር እንዳልፈጸሙ ይናገራል፡፡

ነጋሽ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ራሱን ለማስተዳደር የመረጠው ለሰፈሩ ቅርብ የሆነውን የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታልን ነበር፡፡ እዛም አስከሬንን በመጫንና በማውረድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ እራሱን ሲያግዝ ከቆየ በኋላ የዛሬ 28 ዓመት ገደማ በአስከሬን ምርመራ ክፍል ውስጥ ያሉ ባለሙያዎችን እንዲያግዝ በሚል በጊዜያዊነት ይቀጠራል፡፡

".... አስከሬንን ማየት የሚፈራ ማሰብም የማይፈልግ ብዙ ሰው አለ፡፡ በወቅቱ ለእኔ የሚሆን ሥራ ያገኘሁት ወደ ሆስፒታሉ ለምርመራ የሚመጣ እዛው የሚሞትን አስከሬን መጫንና ማውረድ ነበር፡፡ ይህንን እየሰራሁ ደግሞ ውስጥ ያሉት አስከሬን መርማሪ ባለሙያዎች ተጨማሪ የሰው ኃይል ስላስፈለጋቸው ገብቼ እነሱን እንዳግዝ በኮንትራት ተቀጠርኩ" ይላል፡፡

ሆስፒታሉ በወቅቱ የአስከሬን ምርመራን ያሰራ የነበረው በኩባውያን ባለሙያዎች የነበረ ሲሆን ነጋሽ እነዚህ ሰዎች እንዲያግዝ የዛሬ 28 ዓመት ተቀጥሯል፡፡ ከውጭ ዜጎቹም ልምድ እየቀሰመ ምን እንዴት እንደሚሰራ እየተመለከተ ቆየ፤ በሙያው ላይም ኃላፊነት እየተሰማው ሥራውንም እየወደደው በመሄዱ የውጭ ዜጎቹ ወደሀገራቸው ሲመለሱም በቋሚነት እንደውም ብቸኛ ሆኖ ሥራውን ዛሬ ላይ ለማድረስ ስለመቻሉ ነጋሽ ይናገራል፡፡

ነጋሽ አበራ አስከሬን መርማሪ ሆኖ ላለፉት 28 ዓመታት ሰርቷል አሁንም በዛው ሆስፒታል ከአስከሬን ምርመራ ጋር በተያያዙ በቴክኒሻንነትና በባለሙያነት እያገለገለ ይገኛል፡፡

"........28 ዓመታት በሥራው ላይ መቆየት በጣም ከባድ ነው፤ ከባድ የሚያደርገው ደግሞ ሥራው ከሞተ ሰው ጋር የሚገናኝ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በሰዎች ዘንድም የሚሰጡን ሥዕል ነው፤ በነገራችን ላይ በሀገሪቱ ውስጥ እስከ ዛሬ 4 ዓመት ድረስ ሥራውን እኔና ጓደኛዬ ነን በብቸኝነት ስንሰራው የቆየነው" በማለት የሥራውን አስፈላጊነት ግን ደግሞ የተሰጠውን አነስተኛ ቦታ ይናገራል፡፡

ነጋሽ ሥራውን እንደጀመረ መቋቋም የማይችለው ጭንቀት ገጥሞት እንደነበር ያስታውሳል፤ በተለይም ለመጀመሪያ ጊዜ የሰውን አካል ከፍተህ ጉዳቱን ላይ ተብሎ የተሰጠውን ሥራ የተወጣበትን አጋጣሚ መቼም አይረሳውም፡፡ የገጠመው ፈተና ይህ ብቻ አይደለም ቀን ሲሰራ የዋለው ነገር ሲተኛ እየረበሸው በእንቅልፍ ልቡ ሁሉ መራመድ ጀምሮም እንደነበር ያስታውሳል፡፡

".....የመጀመሪያዎቹ ጊዜያት እጅግ በጣም ፈታኝ ነበሩ ማታ እንቅልፍ አጣለሁ፤ ለመተኛት ብዬ መጠጥ እጠጣ ነበር፤ ይህም ሆኖ ግን ሌሊት ተነስቼ እሄዳለሁ፤ አብረውኝ የሚተኙት ወንድሞቼ አስከሬን እየመሰሉኝ ብዙ አስቸግራቸው ነበር፤ እየቆየሁ ስሄድ ግን ለመድኩትና አሁን ከሥራነቱ ባሻገር እኔን የሚረብሸኝ ነገር የለም" በማለት ይናገራል፡፡

ሥራው አሳዛኝ ነው ሁሌም ከሀዘን ጋር መዋል ይጠይቃል፡፡ ነገር ግን የሕጻናት አስከሬን ሲመጣ ስሜቱ በጣም ይከብዳል፤ እኔም የሚከብደኝ ሕጻናትን መሥራት ነው በማለት አንድ የሚያስታውሰውን ገጠመኝ ይናገራል፤ ".... አባት መኪና እየነዳ ሕጻን ልጁን ከፊት አቁሞት ሲሄድ ልጁ በመስኮት ተፈናጥሮ ወጥቶ አባቱ በድንጋጤ መኪና ነዳበት የዚህ ልጅ አስከሬን ስመለከትና ስሰራው በጣም ነበር የታመምኩት"፡፡

ሌላው ለነጋሽ ፈታኝ የሥራ ወቅት ብሎ የሚያስታውሰው የ1997 ዓ.ም ተቃውሞና ያስከተለው የሕይወት መጥፋት ነው፤ በወቅቱ በሶስት ቀን ብቻ ከ94 በላይ አስከሬኖች ገብተው ስለነበር እነሱን መመርመር ቤተሰብ እንዲለያቸው ማድረግ ፈታኝ ሆኖበት ማለፉን ይናገራል፡፡

"......1997 ዓ.ም የማልረሳው ጊዜ ነበር፤ በጣም በርካታ አስከሬኖች ገብተው ለ10 ቀናት ያህል ከክፍሉ ሳንወጣ ምሳችን እዛው እየመጣልን ነበር የሰራነው፤ የሚገርመው ሰዎች እናንተ አስከሬን መካከል ቁጭ ብላችሁ እየበላችሁ ይሉን ነበር፤ እኛ ግን ደጅ ያለውን ቤተሰብ እንግልት ለመቀነስ ሀዘናቸውን ለማቅለል ነበር ዋጋ የከፈልነው፡፡ በጣም ከባድና የማይረሳ ጊዜ ነው" በማለት ይገልጻዋል፡፡

ከባባድ የመኪና አደጋዎች ተፈጥረው የሰዎች አስከሬን ለምርመራ ይመጣሉ፡፡ ይህ ለነጋሽ ሥራ ፈታኝ በመሆኑና አንዳንድ ጊዜ የሰው አካል ከጥቅም ውጭ የሚሆንበትና ለምርመራም የማይመችበት ሁኔታ ስለሚኖር እንደዚህ አይነት ነገሮችን አስተካክሎ ፈቶ አንስቶ በማስረጃነት ከማቅረብ የዘለለ ሥራ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል



ፎቶ፡ ኢጋፔ ገዩን

አቶ ነጋሽ አበራ

**".....የመጀመሪያዎቹ ጊዜያት እጅግ በጣም ፈታኝ ነበሩ ማታ እንቅልፍ አጣለሁ፤ ለመተኛት ብዬ መጠጥ እጠጣ ነበር፤ ይህም ሆኖ ግን ሌሊት ተነስቼ እሄዳለሁ፤ አብረውኝ የሚተኙት ወንድሞቼ አስከሬን እየመሰሉኝ ብዙ አስቸግራቸው ነበር፤ እየቆየሁ ስሄድ ግን ለመድኩትና አሁን ከሥራነቱ ባሻገር እኔን የሚረብሸኝ ነገር የለም"**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## 28 ዓመታትን...

ከገጽ 6 የዞረ



እንደማይሰራም ነው የሚናገርው።

ምንም እንኳን ነጋሽ ሁልጊዜ ከሰው ሞትና ከአስከሬን ጋር የሚውል ቢሆንም ሰው ነውና በማህበራዊ ሕይወቱም ለቅሶ ሲያጋጥመው ቀብር እንደሚሄድ ይናገራል። ሰዎች ብዙ ጊዜ ያለቅሳል? አያለቅስም? ምን ይሰማዋል? እያሉ እንደሚከታተሉትም ይናገራል። እሱም ቢሆን አንዴ ሰው ከሞተ በኋላ አልቅሶ እንደማይቀብር ነው የሚናገረው። ከዚህ ሁሉ በላይ እሱን የሚያስለቅሰው ወይም የሚያሳዝነው በቁሙ በሕመም በችግር የሚሰቃይና የሚደርስለት ያጣ ሰው ብቻ መሆኑንም ያብራራል።

በ150 ብር የወር ደመወዝ የጀመረው ሥራ ዛሬ ላይ ከትርፍ ሰዓት ክፍያው ጋር ተደማምሮና ተቀናንሶ 5 ሺ ብር የወር ገቢን ያስገኝለታል። ሥራውንም በሳምንት ለሰባት ቀናት የእረፍት ቀንን በዓልን ጨምሮ ሁልጊዜ ይሰራል። ክፍያና ሥራው በፍጹም የማይመጣጠን ራስን ለመለወጥ አይደለም የእለት ኑሮን አሸንፎ ለማለፍ በቂ አለመሆኑን ይናገራል።

እሱና ጓደኛው በብቸኝነት ያለፉትን 28 ዓመታት ሥራውን ቀጥ አድርገው ሰርተዋል፤ ዛሬ ላይ ጳውሎስ ሆስፒታል በመጠኑም ቢሆን ሸክማቸውን አቅሎላቸዋል፤ ነገር ግን ሰውና ሸክላ ተሰባሪ እንደሚሉት ከሁለት አንዳቸው ባይኖሩ ሥራው ስለሚስተጓጎል ችግሮችም ስለሚፈጠሩ የግድ ተተኪ ማፍራት ስለሚያስፈልግ ተጨማሪ ሁለት ሰዎች ተጨምረው እነሱን እያሰለጠኑ ስለመሆኑም ነጋሽ ይናገራል።

በተለያየ ሁኔታ የሞተን ሰው ለምሳሌ የመኪና አደጋ፤ መታነቅ፤ በሰው እጅ መገደል፤ መርዝ የመጠጣት፤ ራስን ማጥፋት፤ የመሳሰሉት የአሟሟት ሁኔታዎች ሁሉ ነጋሽ ጋር ይደርሳሉ፤ እነዚህ አስከሬኖች ደግሞ ትክክለኛ የአሟሟት መንስኤያቸው ብሎም የሞቱበት ሁኔታ ተጣርቶ መቅረቡ ለሟች ቤተሰቦች እረፍት፤ ለፍትህ አካላትም ወንጀለኛን አድኖ ይዞ ተገቢውን ፍርድ ለመስጠት ያግዛልና ሥራውን በጥንቃቄ ማከናወን ይጠበቅበታል። ይህንንም ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ነጋሽ ምን ጊዜም ዝግጁ ስለመሆኑ ነው የሚናገረው።

የሰው በድን አካልን ምን ሆኖ ነው የሞተው ብሎ ለመመርመር ውጫዊውንና ውስጣዊውን አካል አገላብጦ ማየት የግድ በመሆኑን ነጋሽ አስከሬኑን አገላብጦ ያያል። ስብራቱን ጉዳቱን በዓይኑ ይለካል አብሮት ላለው ዶክተር በመናገርም በጽሑፍ እንዲሰፍር ያደርጋል። ይህ አሰራር በአደጋ ሕይወቱን ለሚያጣ ሰው ሲሆን ተመርዞ የሞተን ሰው ደግሞ በድን አካሉን በመክፈት የቱ ጋር ተመረዘ ምን ዓይነት መርዝ ወሰደ የሚለውንም አጣርቶ ሪፖርቱን ያቀርባል።

".....አዎ አስከሬን ወደ ክፍሉ ይመጣል፤ ይታጠባል እኔም ሰውየው ሞተ የተባለበትን ምክንያት ይዤና የሥራ ልምዴን ጨምሬ ውጫዊ አካሉን አያለሁ፤ የሚታየኝን ለዶክተር እናገራለሁ። መክፈት ሲያስፈልግ ደግሞ ከአንገቱ ጀምሮ በመክፈት ውስጥ አካሉ ያለበትን ሁኔታ ተመልክቼ አስተያየቴን እሰጣለሁ። በተመሳሳይ ከወገብ በታች ያለንም ጉዳት ራጅን በመጠቀም ምን ሆኖ ነው የሚለውን እንለካለን"ይላል።

የነጋሽ ሥራ ግን ይህ ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ሞተው አሟሟታቸው አጠራጣሪ ሆኖ እያለ ለምርመራ ወደ ሆስፒታል ሳይሄዱ ይቀበራሉ፤ ጉዳዩ ፖሊስ ጋር ሲደርስ ሌላ ነገር ይመጣና አስከሬኑ ከተቀበረበት ወጥቶ ይመርመር ይባላል፤ ይህም የሚመጣው ወደ ነጋሽ ነው።

" ....የተቀበረን አስከሬን ከመቃብር አውጥቶ ሲመጣ ከባድ ነው፤ እንደ ትኩሱ አስከሬን ሥራውም ቀላል አይደለም ሽታም ይኖራል፤ አንዳንድ አካላትም ረግፈው ይሆናል፤ እና እሱ ብዙ ደስ ባይልም ሥራዬ ነውና ያለውን ነገር አስፈላጊውን ሁሉ ተጠቅሜ እመረምራለሁ፤ ውጤቱንም ለሚመለከተው አካል አደርሳለሁ" ይላል።

የሰውነት አካላት በምርመራ ወቅት ይሰረቃሉ ብሎ ህብረተሰቡ በመፍራት አስከሬን ማስመርመር አይፈልግም ምን ትላለህ? የሚል ጥያቄም ሰንዝረንለት ነበር። ነጋሽ ሲመልስም "......የሥራው ትልቁ ፈተና ይህ ነው። ነገር ግን ሁሉም ሊገነዘብና ሊያውቅ የሚገባው ነገር አንድ አስከሬን ይመርመር ተብሎ ሲመጣ ውጫዊውም ውስጣዊውም አካሉ ላይ ያለውን ጉዳት አይተን ልንመሰክር ነው፤ ሀገራችን ገና በመሆኗ ውስጡን ሳንከፈት ልናይበት የምንችልበት ቴክኖሎጂ የለም፤ ስለዚህ እንከፍታለን፤ ነገር ግን እንደሚባለው አንድም የሰውነት ክፍል ከውስጡ አይወጣም። ይህ በጣም ሊታወቅ ይገባል" ይላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሆስፒታሉ እያንዳንዱን ሥራችንን በካሜራ እየታየ የሚያሰራና ቤተሰብም ምን ተሰራ ወይም ለምን አካሉ ተከፈተብኝ የሚል ጥያቄን ካነሳ ኮምፒውተር ላይ ገብቶ እያንዳንዱን ሂደት መመልከት የሚችልበት አግባብ መኖሩንም ነው የተናገረው።

ሙያው የተከበረና አስፈላጊ ቢሆንም እንደ ማህበረሰብ ያስቀመጥናቸው ነገሮች በመኖራቸው ብሎም አስከሬን የሚባለው ነገር አስፈሪነቱ ብቻ ጎልቶ ስለሚታሰብ እንደ ነጋሽ ያሉ ባለሙያዎችም በህብረተሰቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነትና የሚሰጣቸው ቦታም ዝቅተኛ ነው። ነጋሽም ከጓደኞቹ ጋር ሲዝናና በሥራው ምክንያት ትረባ ምናምንም እንደሚደርስበት ይናገራል። ከዛ ባለፈም ሰው የሞተባቸው አንዳንድ ቤተሰቦች ለምን አስከሬኑ ተከፈተ በሚል ለደብድብም እንደሚጋበዙም ይናገራል።« ስድብማ የየቀኑ ቀለባችን ነው »ይላል ።

እንደ ነጋሽ ያሉ ባለሙያዎች የቅርብ ሰው ሲሞትባቸው ምን ይሰማቸዋል? ፤ ሀዘኑንስ ተቋቁመው ሙያቸውን ማከናወንስ ይችላል ወይ? የሚለው የብዙዎች ጥያቄ ነው።

ነጋሽ ከሥራው ጋር በተገናኘ የራሱ የቅርብ የሆኑ ሰዎች አጋጥመውት ባያውቅም ነገር ግን ጓደኛውና አለቃው የነበሩት ዶክተር ራሳቸውን አጥፍተው አስከሬናቸውን ለመመርመር የሄደበት ሂደት የተፈተነውን ፈተና ግን የማይረሳው ስለመሆኑ ይናገራል።

"......የምናውቀው ሰው ነው አልያም ቤተሰቤ ብዩ ከተልፈሰፈስኩና መሥራት ያለብኝን ነገር በአግባቡ መሥራት ካልቻልኩ ሰውየውን አላገዝኩትም፣ ቤተሰቦቹም በትክክል የሞተበትን ምክንያት የደረሰበትን የጉዳት መጠን አውቀው ተገቢውን ካሳ እንዲያገኙ አላደረኩም ማለት ነው። ስለዚህ የማውቀው፤ የምወደው፤ የቅርቤ የምለው ሰው እንኳን ቢሆን ሥራዬን በአግባቡ ተወጥቼ ደሙን መመለስን ነው የማስበው የምሠራውም በዚሁ መልክ ነው " ይላል።

ሥራው በጣም ከባድ የሚያደርገው ሰዎች ተላላፊ በሆነ በሽታ ሲሞቱ የሚያስከትለው ችግር ነው የሚለው ነጋሽ በተለይም በሳንባ በሽታ የተያዙ ሰዎችን መመርመር ብዙዎችን ለሳንባ በሽተኝነት እንደሚያጋልጥ ይናገራል። ከእነሱ ቀደም የነበሩና እነሱ የተኳቸው ባለሙያዎች አብዛኞቹ በሳንባ በሽታ ስለማለፋቸው ያስታውሳል።

".....ከሰው ወደሰው የሚተላለፉ በሽታዎች ለምሳሌ የጉበት በሽታ ተላላፊ በመሆኑ ክትባት እንድንከተብ ይደረጋል። ነገር ግን የቲቢ በሽታን የምንከላከልበት መንገድ ባለመኖሩ 6 ያህል ቴክኒሻኖች ሞተውብናል። ይህ የሚሆነው አስከሬን ለመመርመር ሲከፈት የሚወጣ ትንፋሽ አለ፤ የቲቢ በሽተኛ ሲሆን ያ ትንፋሽ በሽታውን ይዞ ይወጣል፤ በዚህ ምክንያት በሕመሙ የመያዝ እድል ይኖራል። ሌላው ደግሞ ቤቱ ቀዝቃዛ እንዲሆን ስለሚፈለግና ፍሪጀችም ስላሉ ለበሽታው ተጋላጭነታችን በእጥፍ የጨመረ ነው" በማለት ሁኔታውን ያስረዳል።

ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት የሆነው ነጋሽ ባለቤቱ ስለሥራው ሁኔታና ባህርይ እንደምታውቅ ይናገራል። ነገር ግን ከእሷ በፊት የሴት ጓደኛ ሲተዋወቅ ይቸገር እንደነበርና እንደውም ሙያውን ሳይናገር የቅርጫት ኳስ አሰልጣኝ ነኝ ሁሉ በማለት ለመተዋወቅ ስለመሞከሩ ያስታውሳል።

"......ባለቤቴን ከማግባቴ በፊት ከአንዲት ወጣት ጋር ተዋውቀን ፍቅር ጀምረን ነበር፤ ስተዋወቃት የቅርጫት ኳስ አሰልጣኝ ነኝ አልኳት፤ አንድ ቀን ግን የምኖርበት ሰፈር መጥታ " ነጋሽ የሚባል የቅርጫት ኳስ አሰልጣኝ ታውቃላችሁ ወይ" ብላ ስትላቸው አዎ ያውልሽ እያሰለጠነ ነው ብለው ወደምሰራበት ይዘዋት መጡ፤ እኔ ስትገባ አይቻታለሁ እሷ የሥራ ልብሴን ስለለበስኩ አላወቀችኝም፤ ግን የምሠራውን ነገር ስለተረዳች ደውላ የእኔ አሰልጣኝ ብላ በመቆጣት ተሳድባ በዛው ቀረች " በማለት በፍቅር ሕይወቱ ያጋጠመውን ይናገራል።

ባለቤቱ ግን የሰፈሩ ልጅና አብሮ አደጉ በመሆኗ ሥራውንም ጠንቅቃ ስለምታውቅ ወደፍቅሩም ትዳሩም ለመግባት ብዙም አልተቸገረም፤ አሁንም አብረው ልጆቻቸውን በጥሩ ሁኔታ እያሳደጉ መሆኑን ይናገራል።

**መልዕክት**

ህብረተሰቡ ሊያውቅ የሚገባው ነገር አስከሬን ምርመራ የራሱ የሆኑ ሂደቶችና የሥራ ሥነ ሥርዓት (ዲሲፕሊን) እንዲሁም ሕግ ያለው ነገር መሆኑን ነው። ሰዎች ምንም ያልሆነን አካል ይዘው መጥተው እንዲመረመርላቸው ሲጠይቁ እኛ ደግሞ ከፍተን ያለውን ነገር አይተን ነው መልስ መስጠት የምንችለው። በዚህ መካከል የተከፈተው የውስጥ አካሉን ሰርቀውት ነው ብሎ ማሰብ ስለሥራው ካለማወቅ የመነጨ በመሆኑ እኛ የሚሰማን ጥፋተኝነት የለም። እኔም ብሆን ሥራውን ባላውቀው ልለው የምችለው ነገር ይህን ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሁሉም ሰው ማወቅና መረዳት ያለበት ከአስከሬን ላይ የሚወሰድ ምንም ዓይነት የሰው አካል አለመኖሩን ነው።

አስከሬን የሚከፈተውም ድንገት ለሞት ያበቃው ልቡ ነው፣ ሳንባው ወይስ ተመርዞ ነው የሚለውን ለማየት ሲሆን፤ ፖሊስ የሚያመጣቸውን አስከሬኖች ደግሞ ሰው ነው የገደለው? እንዴት ሞተ? በመርዝ?፤ በማነቅ? ወይስ ሌላ የሚለውን ለማየት ነው። መኪና አደጋ ሲሆን ምኑን መቶት?፣ ምን ያህል ጉዳት አድርሶበት ሞተ? የሚለውን ለማጣራትና ሕግ የራሱን ውሳኔ እንዲሰጥ ለማስቻል ስለመሆኑ መናገር እፈልጋለሁ በማለት ሃሳቡን ቋጭቷል።

የነጋሽ ሥራ ግን ይህ ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ሞተው አሟሟታቸው አጠራጣሪ ሆኖ እያለ ለምርመራ ወደ ሆስፒታል ሳይሄዱ ይቀበራሉ፤ ጉዳዩ ፖሊስ ጋር ሲደርስ ሌላ ነገር ይመጣና አስከሬኑ ከተቀበረበት ወጥቶ ይመርመር ይባላል፤ ይህም የሚመጣው ወደ ነጋሽ ነው::

# የክልሉ ቱሪዝም እንዲያንሰራራ-ተስፋ ሰጪ ጅምሮች

**ዳግም ከበደ**



የትግራይ ክልል የቱሪዝም ዘርፍ እንዲያንሰራራ የሚያስችሉ ተግባሮች እየተከናወኑ ናቸው

ኢትዮጵያ የቀደምት ዘመን ስልጣኔ ተምሳሌት፣ የራስ ባህል፣ ማንነት እንዲሁም ሉዓላዊ ግዛት ያላት ጥንታዊ ሀገር ነች። ለዘመናት የራሷን ሀገረ መንግሥት መስርታ በቀኝ ገዢ እጅ ሳትወድቅ አሁን ላይ ከመድረሷም ባሻገር የብዝሀ ባህል፣ ሕዝብ፣ ቋንቋ ብሎም የጥበብና እውቀት መፍለቂያ ምንጭ እንደሆነች የታሪክ መዛግብትና የዓለማችን ጸሐፍት ይመሰክሩላታል። እነዚህን መገለጫዎች እንድትይዝ ካስቻሏት የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ ደግሞ የትግራይ ክልል አንዱ ነው።

የትግራይ ክልል በርካታ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሃብቶች የታደለ አካባቢ ነው። ጥንታዊ ቤተ መቅደሶች፣ የአክሱም ጥንታዊ ሃውልቶች፣ ከ4ኛው እስከ 15ኛው ክፍለ ዘመን እንደተሰሩ የሚነገርላቸው ከ120 በላይ የሚሆኑ ከአለት ድንጋይ ተፈልፍለው የተሰሩ ውቅር አብያተ ክርስትያናትና ገዳማት እንዲሁም ሌሎች በርካታ ታሪካዊና አርኪኦሎጂካዊ ስፍራዎች የሚገኙበት የኢትዮጵያ ክፍል ነው።

ክልሉ በኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ግዙፍ ድርሻ ቢኖረውም፣ በሰሜኑ ክፍል የተካሄደውን ጦርነትና የሰላም እጦት ተከትሎ ተቀዛቅዞ ቆይቷል። በአካባቢው ሲካሄድ የነበረው ጦርነት እንዲቆምና ሰላም በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ስምምነት መደረሱ ይታወሳል፤ ይህን ተከትሎ በተከናወኑ ተግባሮች በሰላም በኩል መሻሻሎች እየታዩ መምጣቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ።

የክልሉ የቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲያንሰራራ ለማድረግ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችም የዚህ ስምምነት አካል ናቸው። ከሰሞኑ በክልሉ የተካሄደ አንድ መድረክም ይህንኑ ጉዳይ የሚያጠናክር ሆኖ አግኝተነዋል። የቱሪዝም ዘርፉን በበላይነት የሚመራው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በትግራይ ክልል የቱሪዝም ትግበራዎችን ዳግም ለማስጀመርና ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ ለመግባት ሥራዎች መጀመራቸው ተጠቁሟል፤ ሚኒስቴሩ ከፍተኛ አመራሮቹን ወደ አካባቢው መላኩን ተመልክቷል።

የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ፣ ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ስለሺ ግርማ፣ የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን አመራሮች በመቀሌ በመገኘት ከትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት ጌታቸው ረዳ እና ከክልሉ የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ጋር መክረዋል። በክልሉ የቱሪዝም፣ የቅርስ እና ፓርኮች ሀብቶች ልማት፣ ፕሮሞሽን አሁናዊ ሁኔታ እና በቀጣይ በሚከናወኑ ተግባራት ዙሪያ በመወያየት በየደረጃው በሚሰሩ ተግባራት ዙሪያ መግባባት ላይ የደረሱ ሲሆን፣ በመቐለ ከተማ የሚገኘውንም የአጼ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ጉብኝት አድርገዋል።

ይህንንም ተከትሎ የቱሪዝም ሚኒስቴር በትግራይ ክልል በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው ግጭት ምክንያት ቆሞ የነበረውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ዳግም ለማስጀመርና ለማነቃቃት የሚያስችል ስልጠና መስጠቱን የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሕዝብ ግንኙነት የሥራ ክፍል አስታውቋል።

በፕሮግራሙ ማስጀመሪያ መርሀ ግብር ላይ ተገኝተው የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የትግራይ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር አፅብሃ ገብረ እግዚአብሔር ጦርነቱ ከቆመ በኋላ እንደዚህ አይነት መድረክ ሲዘጋጅ ይህ የመጀመሪያ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በዚህ መድረክ ለዘርፉ በርካታ ብዙ ፋይዳ ያላቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እንደሚሰጡ ጠቁመዋል። ቱሪዝም ሚኒስቴር በዚህ ወቅት ይህንን የስልጠና መድረክ በማዘጋጀቱና ከክልሉ ጎን በመሆኑ አክብሮትና ምስጋናቸውን ገልፀዋል።

ሌላው በስልጠና መድረኩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ በግጭቱ ምክንያት የክልሉ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ተቋርጦ እንደነበር አስታውሰዋል። ተቋርጦ የነበረው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ዳግም እንዲያንሰራራ እና እንዲነቃቃ ለማድረግ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በቱሪዝም ዘርፎች ላይ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን እንደሚሰጥ ተናግረዋል። ህልውናቸውን በቱሪዝም ዘርፍ ላይ አድርገው ይኖሩ ለነበሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ይህ መድረክ ወሳኝ መሆኑንም ነው ያመለከቱት፤ ከነሐሴ 16 ጀምሮ የሚከበሩትን የአሸንዳ በዓላት በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የውጭ ቱሪስቶች እንዲጎበኙዋቸው ለማድረግ ክልሉ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እና የማስተዋወቅ ሥራ እንዲሰራ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በትግራይ ክልል ለቱሪዝም ባለሙያዎች ዘርፉ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን፣ ስልጠናዎቹ በቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ስትራቴጂክ አስተባባሪ አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፣ አቶ ይስፋልኝ ሀብቴ የፕሮሞሽን መሪ ስራ አስፈፃሚ እንዲሁም አቶ መቅደላ መሰጠታቸው ተገልጿል። ስልጠናው በዋናነትም የተቀዛቀዘውን የክልሉን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ማነቃቃት፣ ከመልሶ ግንባታ፣ ከመዳረሻ ልማትና ከቅርሶች ጥገና ጋር የተያያዙ ነጥቦች የተነሱበት ነበር። በተጨማሪ ስልጠናው በቱሪዝም ሚኒስቴር ባለሙያዎች እና በዩኒቨርሲቲ ምሁራን በቱሪዝም መሠረተ ልማት፣ የቱሪዝም ግብይቱን ዲጅታላይዝ በሆነ መንገድ በቴክኖሎጂ በመታገዝ መዳረሻዎችን ከማስተዋወቅ አንፃር፣ የቅርስ ጥገና እና የአገልግሎት ፈላጊዎች የብቃት አሰጣጥ ሁኔታን እና መመሪያዎቹን የተመለከቱ ሀሳቦች ተነስተውበታል።

የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው የቱሪዝም ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሥራ አስፈፃሚ አቶ ዓለማየሁ ጌታቸው በመድረኩ መልካም ውጤት መመዝገቡን ገልጸውልናል። በተለይ ተሳታፊዎቹ በስልጠናው ወቅት የሰጡትን አስተያየት መሠረት አድርገው ሲገልፁ፣ ስልጠናው እንዳስደሰታቸው እና የተዳከመውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ለማነቃቃት እድል እንደሚፈጥርላቸው ተናግረዋል ሲሉ አቶ ዓለማየሁ ተናግረዋል። በዘርፉ ተሰማርተው ኑሮአቸውን የሚመሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ወደ ሥራቸው ለመመለስ እንደሚያስችላቸው ነው ያስታወቁት።

"የክልሉ የቱሪዝም እንቅስቃሴ በኮቪድ ወረርሽኝና በጦርነት ምክንያት ቆሞ ነበር" የሚሉት የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አስፈፃሚው፤ በዚህ ምክንያት የተዳከመውን የቱሪዝም ዘርፍ ለማነቃቃትና የተፈጠረውን መልካም አጋጣሚ ለመጠቀምና በይፋ ሥራዎችን ለማስጀመር የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን ይናገራሉ። በመጀመሪያ በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ (የተበላሹ) የመዳረሻ ቦታዎችና የሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪው እንዲያገግምና ወደ ሥራ የሚገቡበትን መንገድ ለመፈለግ የውይይት እና የስልጠና መድረክ ማዘጋጀት ማስፈለጉን ይናገራሉ።

ሥራ አስፈፃሚው፤ በዘርፉ ከወደመው ሃብትና ከቆመው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ውጭ በሰው ሀብቱ ላይም አሉታዊ ተጽእኖ አርፏል ይላሉ፡፡ ይህን በማነቃቀት ላይም መሥራት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ። በተለየ ከሥራ ውጭ ሆኖ የቆየው የሰው ኃይልን ማነቃቃት እንዲሁም ሙያዊ ስልጠና መስጠት ማስፈለጉን አንስተዋል። በዚህ ምክንያት ይህ ሥራ በቅድመ ትግበራ ሥራው ላይ መካተቱን ይናገራሉ። ከዚህ መነሻ 450 የሚደርሱ የቱሪዝም እና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ባለሙያዎችን፣ የሆቴል ባለቤቶችን፣ ሥራ አስኪያጆች፣ የቱር ኦፕሬተር ባለቤቶችንና አስጎብኚዎችን እንዲሁም በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ያሉ ባለሙያዎችን ያካተተ ስልጠና መሰጠቱን ይገልፃሉ።

ሥራ አስፈፃሚው እንደሚሉት፤ ወደዚህ ትግበራ ከመገባቱ በፊት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተጠሪ ተቋም የሆነው የቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን እና የትግራይ ክልል የባህልና ቱሪዝም ቢሮ በጋራ በመሆን ቡድን አዋቅሮ በቅርሶቹ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የደረሱ ጉዳቶችን ለመለየት ተችሏል። አንዳንዶቹ በቀጥታ በጦርነቱ ምክንያት የደረሱ ጉዳቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ የባለሙያ ክትትል ባለማግኘታቸው ምክንያት የደረሱ ናቸው። እነዚህን ጉዳቶች ከመለየት ባሻገር በቂ ጥገናና እንክብካቤ የሚደረግበትን መፍትሔ ለማስቀመጥ ከስልጠናው ጎን ለጎን ውይይትና ምክክር እየተደረገ እንደሚገኝ አስረድተዋል።

የቅርስ ጥገና ሥራው ከፍተኛ ወጪን እንደሚጠይቅ የሚናገሩት ሥራ አስፈፃሚው፤ ከዚህ ባሻገር የሰው ኃይልና ሰፊ ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑን ይናገራሉ። ይህንን አሟልቶ ወደ ትግበራ ለመግባት ከዩኒቨርሲቲዎች (አክሱም፣መቀሌ) እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻዎችም በጋራ የሚሰሩበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተጨማሪ የፋይናንስ አቅምን ለማጠናከር የድጋፍ ማፈላለግና የፋይናንስ ምንጭ ልየታዎች መደረጋቸውን ይገልፃሉ።

"ከቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ በተጓዳኝ ወደ ክልሉ የቱሪስት ፍሰቱን ለማስጀመር እየሰራን ነው" የሚሉት የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አስፈፃሚው፤ የውጪ ጎብኚዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ በብዛት ወደ ክልሉ እንዲሄዱ ማድረግ ባይቻል እንኳን፤ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ቁጥር እንዲጨምርና ዘርፉ መነቃቃት እንዲችል ለማድረግ ልዩ ልዩ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባር ላይ ለማዋል እየተሰራ መሆኑን ይናገራሉ።

ሥራ አስፈፃሚው እንደሚሉት፤ የክልሉንና የፌዴራል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን ግንኙነት እና የሥራ ክፍፍል በጠበቀ ሁኔታ ለማስኬድ የሚያስችሉ ተግባራት ተጀምረዋል። በተለይ በክልሉ በፌዴራል ደረጃ የሚተገበሩ እንደ ሰው ኃይል አቅም ግንባታ፣ የሆቴሎች፣ የቱር ኦፕሬተሮች እና አስጎብኚዎች ፈቃድና ደረጃ መስጠት ጋር ተያይዞ ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ኃላፊነቱን ለመወጣትና ግንኙነቱን ለማጠናከር እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል። በተለይ የውጪ ግንኙነቶችን በማድረግ የትግራይ ክልል የቱሪዝም መዳረሻዎችን የሚጠቅም ፕሮጀክቶችን ለማስጀመርም በተመሳሳይ እየተሰራ ነው።

"በትግራይ ክልል የቱሪዝም ዘርፉ እየተነቃቃ ነው። ከልዩ ልዩ አካባቢዎችም ወደ ክልሉ የሚገቡ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች አሉ" የሚሉት ሥራ አስፈፃሚው ይህን በጎ ጅምር ማስፋት ላይ በጋራ ለመሥራት የተጀመሩት ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም ገልጸዋል። በቅርቡ በክልሉ በድምቀት የተከበረው የአሸንዳ የሴቶችና ልጃገረዶች በዓል ለቱሪዝም ዘርፉ መነቃቃት ልዩ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትም ገልጸዋል። በተለይ በዲጂታል ሚዲያው ክልሉ ላይ ያለውን ሰላማዊ እንቅስቃሴ፣ የበዓሉን ድምቀትና ሥርዓት አስመልክቶ እየወጡ ያሉ መረጃዎች ዳግም ዘርፉን ለማነቃቃት እየተሰሩ ያሉ ተግባራትን እንዲጨምሩ የሚያግዝ እንደሆነ ይናገራሉ።

ሥራ አስፈፃሚው የክልሉን የቱሪዝም ዘርፍ ለማነቃቃት ከሚደረገው ጥረቶች መካከል አንዱ የማህበራትን አቅም መገንባት እንደሆነ ተናግረዋል። በተለይ በአስጎብኚነት፣ በቱር ኦፕሬተርነትና በቱሪዝም ምርት አቅራቢነት ላይ የተሰማሩ እና በማህበራት የተደራጁ አካላት የክልሉን ቱሪዝም ቀድሞ ከነበረበትም በተሻለ መልኩ እንዲነቃቃ ለማስቻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ገልጸዋል። በዚህ ምክንያት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች፣ የውይይት መድረኮችና የልማት ሥራዎች እነሱን መሠረት አድርገው እየተቀረጹና ወደ ተግባር እየተለወጡ መሆኑን አስረድተዋል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ለሁለት ዓመታት በተካሄደው የሰሜኑ ክፍል ጦርነት ምክንያት ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ የቱሪዝም ዘርፉ ቆሞ ነበር። በተለይ በትግራይ ክልል የመዳረሻ ሥፍራዎች በጦርነቱ ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል። ቱሪዝምን መሠረት አድርገው የእለት ጉርሳቸውን የሚያገኙ ዜጎች ሥራ አጥ ሆነው ቆይተዋል። ሆቴሎች፣ ቱር ኦፕሬተሮችና መሰል የዘርፉ አንቀሳቃሾች ሥራቸውን ለማቋረጥ ተገደዋል።

ይህ ለሁለት ዓመታት ቢዘልቅም በፕሪቶሪያው ስምምነት የቱሪዝም ዘርፉ ዳግም ወደ ማንሰራራት እየመጣ ይመስላል። ይህን ጅምር መሬት ላይ ለማውረድ የፌዴራልና የክልሉ ቱሪዝም ዘርፍ አመራሮች የያዙትን ርብርብ አጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ወራሪን ያጨደው የመድፉ ጌታ

**ዋለልኝ አየለ**

የሰለጠኑ ናቸው በሚባሉ ሀገራት አንዲት ትንሽዬ ታሪክ የሰራ ሰው ከውልደቱ እስከ ሞቱ ያሉ ታሪኮቹ ይጻፋሉ። ስሙን ወደ በይነ መረብ ስናስገባ ለማንበብ እስከሚያታክተን ረጃጅም ማብራሪያዎች ይመጣሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ይህ ብዙም የለም። የአንድ ጀግና ስም ወደ በይነ መረብ ብናስገባ የምናገኘው ጽንፍ የያዙ ብሽሽቆችን ነው። በዚህ ሁኔታ ኢትዮጵያን ያህል ታላቅ የጀግና ሀገር የጀግኖቿን ታሪክ እያደበዘዝነው ነው። እነዚህ ጀግኖች ግን ክብሯ የተጠበቀ ኢትዮጵያን አስረክበውናል።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ከ113 ዓመታት በፊት ልክ በዛሬዋ ቀን ነሐሴ 21 ቀን 1902 ዓ.ም የተወለደውን አርበኛ በቀለ ወያን እናስታውሳለን።

ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የተከናነበችውን ሽንፈት ለመበቀል ለአርባ ዓመታት ያህል ስትዘጋጅ ከኖረች በኋላ በየጊዜው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በባህል መስክ የተፈራረመቻቸውን የሰላምና የትብብር ውሎችና በመንግሥታትቱ ማህበር አባልነቷ የገባቻቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ሁሉ በመጣስ ውሎችን በጠመንጃ አፈሙዝ መቅደድ ጀመረች።

እንዲህ እንዲህ እያለች በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን ወረረች። በሀገሩና በነፃነቱ የማይደራደረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የፋሺስትን አገዛዝ ‹‹አሜን›› ብሎ አልተቀበለውም። ይልቁንም ጨርቄን ማቄን ሳይል ‹‹ጥራኝ ዱሩ›› ብሎ ለነፃነቱ መፋለም ጀመረ። የኢጣሊያ ወራሪ ኃይልም አንዲትም ቀን እንኳን እፎይ ብሎ ሳይቀመጥ ከአምስት ዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ ሌላ የሽንፈት ማቅ ለብሶ ከኢትዮጵያ ምድር ተባረረ። በዚህ አስገራሚና አኩሪ የመስዋዕትነት ጉዞ ውስጥ ደማቅ የጀግንነት ታሪክ ከፃፉና ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ከተጋደሉ እልፍ የኢትዮጵያ ጀግኖች መካከል አንዱ ዝነኛው የመድፍ ተኳሽ አርበኛ ደጃዝማች በቀለ ወያ ናቸው።

ሕፃኑ በቀለ አማርኛ መማር እንዳለበት ያመኑት ቤተሰቦቹ፣ መምህር ተቀጥሮለት ቤቱ ውስጥ አማርኛን ተምሮ አጠናቀቀ። እድሜው 16 ሲሆንም ወደ አጎቱ ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ ዘንድ ሄዶ እንዲኖር ስለተወሰነ ወደ አጎቱ ዘንድ ሄደ። በሥነ ሥርዓት አክባሪነቱ፣ በቅንነቱ፣ በጨዋነቱ፣ በእርጋታውና በአስተዋይነቱ የአጎቱን የደጃዝማች ገብረማርያምን ቀልብ ለመሳብ ጊዜ አልፈጀበትም። እድሜው ከፍ ሲልም የአጎቱ እልፍኝ አስከልካይ ሆነ።

ደጃዝማች ገብረማርያም የሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ በነበሩበት ወቅት በቀለ ‹‹ሻቃ›› የሚል የማዕረግ ስም ተሰጥቶት በረዳት ወታደርነትና በአስተዳደር ሥራ አገልግሏል። በኋላም ደጃዝማች ገብረማርያም የሀገር ግዛት ሚኒስትር ሆነው ሲሾሙ በቀለ አብሯቸው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የታንክ መስበሪያ መሣሪያ አጠቃቀምን ተማረ። የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን መውረር ሲጀምር ወጣቱ በቀለ ሀገሩን ከወራሪ ኃይል በመከላከል ሉዓላዊነቷን የማስጠበቅ ኃላፊነት እንዳለበት ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ለእናት ሀገሩ ክብር ለመፋለም ታጠቀ።

ወረራው እንደተጀመረ ሻቃ በቀለ ወደ ሰሜን ግንባር ዘመተ። በመቀጠልም በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ወደ ደቡብ ግንባር በመሄድ ከአጎቱ ከደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ ጋር በጠላት ላይ አንጸባራቂ ድሎችን መቀዳጀት ቻለ። በወቅቱ ደጃዝማች ገብረማርያም ጦራቸውን አሰልፈው ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመጓዝ ቆቦ ደርሰው ቦታውን ከተቆጣጠረው ግንባር ቀደም የጠላት ኃይል ጋር ውጊያ ገጥመው የጠላት ጦር ለቀጣዩ ውጊያ እንዲረዳው በማሰብ የዘጋውን በር ማስከፈት የቻሉ ቢሆንም በደቡብ በኩል የነበረው የጠላት ወረራ የበረታ ስለነበር ደጃዝማች ገብረማርያም ከሰሜን ወደ ደቡብ ሄደው ከራስ ደስታ ዳምጠው ጋር ሆነው ጠላትን እንዲመክቱ በንጉሠ ነገሥቱ በመታዘዛቸው ወደ ደቡብ ግንባር ሄደው ነበር።

በግንቦት 1928 ዓ.ም ደጃዝማች ገብረማርያም ድኑን በተባለ አካባቢ በጠላት ጦር ላይ የሁለት አቅጣጫ ጥቃታቸውን አፋፍመው ድል ሲቀዳጁ አብረዋቸው ከተሰለፉት የጦር አዝማቾች መካከል አንዱ ሻቃ በቀለ ነበር። በዚህ ጦርነት ላይ የደጃዝማች ገብረማርያም ታላቅ ወንድም ደጃዝማች ኡርጋ ጋሪ እና ፊታውራሪ ተሰማ አብዲ አብረው ነበሩ። በዚህ ጦርነት ድል የጨበጠው የደጃዝማች ገብረማርያም ጦር የፋሺስት የጦር መኮንኖችንና ወታደሮችን ከመደምሰሱም በተጨማሪ መትረየሶችን መማረክ ችሏል።

አርበኛና የታሪክ ጸሐፊ ቀኛዝማች ታደሰ ዘወልዴ ‹‹ቀሪን ገረመው›› በሚለው የአርበኞች ታሪክ መጽሐፋቸው ላይ በቀለ ወያ በወቅቱ ስላከናወነው አኩሪ የጀግንነት ታሪክ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል ...

‹‹ ... የጠላት ታንክ የወገንን ጦር በማጥቃቱ ደጃዝማች ገብረማሪያም ጋሪ በጣም ያዝኑ ነበር። አንድ ቀን አምስት ታንኮች በመደዳ ሆነው ጦሩን እያጠቁ ሲመጡ ‹በቀለ ያንተ ብልሃት ለመቼ ሊሆነን ነው?› እያሉ ደጃዝማች ገብረማሪያም ጋሪ ሲያዝኑ በቀለ ዝም ብሎ ይመለከት ነበር። ታንኮቹ ጠጋ ብለው በደንብ ሲታዩት በመድፍ የመጀመሪያውን አኮማተረው፣ የኋለኛውን ደገመው። እንደዚሁ አድርጎ በአምስት ደቂቃ ውስጥ አምስቱንም ታንኮች አቃጥሎ ሲነዱ ‹ደጃዝማች ሄደው እሳት ይሙቁ› አላቸው ... ›› በማለት የወቅቱን የጀግንነት ሥራውን በከፍተኛ አድናቆት ጽፈዋል።

በመቀጠልም ከሰኔ 1928 ዓ.ም እስከ የካቲት 1929 ዓ.ም ድረስ በብዙ የጦርነት ዘመቻዎች ላይ ተሳትፎ ድሎችን አስመዝግቧል። ለአብነት ያህል በአለታ ወንዶ አካባቢ ተፈሪ ኬላ በተባለው ቦታ፣ በአርቤጎና፣ በዳኤላ ጭሪ፣ አርሲ ውስጥ ሂበኖ በተባለው ቦታ፣ በሶዶ እና በዝቋላ አካባቢዎች በተካሄዱ ውጊያዎች ከጠላት ጦር ጋር እልህ አስጨራሽ ፍልሚያዎችን አድርጓል። በተለይም ደባ ስሬ በተባለው አካባቢ በተካሄደው ጦርነት አጎቱ ደጃዝማች ገብረማርያም ቢቆስሉም ሻቃ በቀለ በርካታ የጠላት ታንኮችን በመድፉ በማውደም የማይረሳ የጀግንነት ታሪክ ሠርቷል።

ኅዳር 8 ቀን 1929 ዓ.ም ደጃዝማች ገብረማርያም በመትረየሳቸውና ‹‹ገላግሌ›› በሚባለው ባለጋሻ መድፍ እየታገዙ በጠላት ላይ ጥቃት ከፈቱ። በዚህ ጥቃት ከሙቶ የሚበልጡ የጣሊያን ወታደሮች ሲደመሰሱ ጫካውን ተገን አድርጎ ካመለጠው የሀገር ተወላጅ ባንዳ በስተቀር አብዛኛው ባንዳ እዚያው ጫካ ውስጥ ቀርቷል። በኋላ እንደተረጋገጠው ደግሞ አንድ የጣሊያን የጦር ጀኔራልም በውጊያው ሞቷል። ከዚህ ውጊያ በኋላ የጣሊያን ጦር የማጥቃት ዘመቻ ቢያደርግም ምንም ውጤት ስላላመጣለት በቦታው የነበረው ጦር አዛዥ ጀኔራል ጀሎዞ ለማርሻል ሩዶልፎ ግራዚያኒ ‹‹የተፈሪ ኬላን በር ጥሼ ወደመሐል ሀገር ወደ ይርጋለም ማለፍ አልቻልኩም፤ ስለዚህ ወታደሮቼን ይዤ ወደኋላ ማፈግፈግ ግድ ሆኖብኛል›› በማለት መልዕክት ልኮለት ነበር።

በደጃዝማች ገብረማርያም የማጥቃት ርምጃ የተጎዳው የጣሊያን ጦር እንደገና ተጠናክሮ ማጥቃት ጀመረ። ደጃዝማች ገብረማርያምም በወንድማቸው ቀኛዝማች ኡርጋ ጋሪና በሻቃ በቀለ ወያ ታግዘው የሲዳሞን ጦር ይዘው የጠላትን እግረኛ ጦር ለአራት ተከታታይ ቀናት መመከት ችለዋል።

በሰሜንና በምስራቅ በኩል የማጥቃት ዘመቻ የከፈተው የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ዋና ከተማው አዲስ አበባ ድረስ ዘልቆ መግባት ቢችልም በደቡብ በኩል የነበረው ጦር ግን ከነራስ ደስታ ዳምጠው እና ከነደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ በኩል በገጠመው የመከላከልና የማጥቃት ዘመቻ ምክንያት ወደ አዲስ አበባ መድረስ ስላልቻለ የግንባሩ ጦር አዛዥ ጀኔራል ጀሎዞ እና ዋናው የአስተዳደሩ ተወካይ ማርሻል ሩዶልፎ ግራዚያኒ ለራስ ደስታና ለደጃዝማች ገብረማርያም ልመና፣ ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ የተቀላቀሉባቸው ደብዳቤዎችን ጽፈውላቸው ነበር።

ጥር 1 ቀን 1929 ዓ.ም ሻንቆ በተባለው ቦታ ላይ በተደረገው ውጊያ ኢትዮጵያውያን በጠላት እግረኛ ጦር ላይ ከፍተኛ ድል ቢቀዳጁም የጠላት ጦር በአውሮፕላን የሚያዘንበውን ቦምብና መርዝ ግን መቋቋም አልተቻለም። በመሆኑም አርቤጎናን በመልቀቅ ብዙ የወገን ጦር ወዳለበት ወደ ባሌ ግዛት ለመሄድ ተወሰነ። ውጊያው በመንገድ ላይም አላባራም ነበር። የወገን ጦር መንገድ የዘጋበትን የፋሺስት ጦር በመውጋት መንገድ እያስከፈተ ዘለቀ።

ጥር 20 ቀን 1929 ዓ.ም ራስ ደስታ ዳምጠው፣ ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ፣ ደጃዝማች በየነ መርዕድ፣ ደጃዝማች በዛብህ ስለሺ እና ፊታውራሪ ሽመልስ ሀብቴ ጦራቸውን ይዘው እነርሱም መድፍ ጠምደው በተሰለፉበት ውጊያ ላይ ሻቃ በቀለ፣ ከአጎታቸው ከደጃዝማች ገብረማርያም ጋር ሆነው ታላቅ የጀግንነት ሥራ ሰርተዋል። የሚያስገርመው ነገር በዚህ ጦርነት ላይ ደጃዝማች ገብረማርያም በወቅቱ አመርቅዞ እየጠዘጠዘ ያሰቃያቸው የነበረውን ቁስላቸውን ከምንም ሳይቆጥሩ የታጠቁትን ሱሪ ወደላይ በመሰብሰብ ያለጫማ እየተራመዱ በያዙት ግንባር በኩል በግራና በቀኝ እየተሽከረከሩ ዝናር ሙሉ ያጎረሱትን መትረየስ በጠላት በኩል በማስገባት በር ማስከፈታቸውና በጠላት ጦር ላይ ትልቅ ጉዳት ማድረሳቸው ነው። በዚህ ተጋድሎ እነሻቃ በቀለና ተዋጊዎቻቸው አካባቢው በጠላት እጅ እንዳይወድቅ ከማድረጋቸውም ባሻገር በጠላት ጦር ላይ ከበድ ያለ ጉዳት ማድረስ ችለዋል።

የካቲት 10 ቀን 1929 ዓ.ም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ወደ ቡታጅራ በሚወስደው መንገድ ላይ በሚገኘው የፋሺስት ጦር ላይ ጥቃት ተከፈተ። ጠላት ያላሰበው ጥቃት ስለነበርም ክፉኛ ተጎዳ። ለበቀል ርምጃ የተነሳው የጠላት ጦር ርምጃ መውሰድ ሲጀምር እልህ አስጨራሽ ውጊያ ተካሄደ። ራስ ደስታ ዳምጠው ጥቂት ወታደሮችን ይዘው ወደ መስቃን ሄዱ። ቀኛዝማች ኡርጋ ጋሪ፣ ቀኛዝማች በየነ ጉደታ እና ሻለቃ በቀለ ወያ ያሉበት ቀሪው ጦር ደጃዝማች ገብረማርያምን አጅቦ ወደ ማረቆ ወደሚገኘው ጎጌቲ ገብርኤል ሲያመራ የጠላት ጦር ክትትሉን ስላላቋረጠ ጎጌቲ ገብርኤልን ከብቦ ያዘ። ደጃዝማች ገብረማርያምም እየመከቱ ሚልኮ ማርያም ደረሱ። ይህ ውጊያ የመጨረሻው እንደሚሆን ቀድመው ያወቁት የዓድዋው ጀግና ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ አብረዋቸው የነበሩት አርበኞች ለኢትዮጵያ ነፃነት እንዲፋለሙ ተናገሩ። ሻቃ በቀለ ወያንና ቀኛዝማች በየነ ጉደታን አቅርበው በምንም ዓይነት ሁኔታ እጃቸውን እንዳይሰጡ መክረውና መርቀው ካሰናበቱ በኋላ የጠላትን ወታደር ሲያጋድሙ ውለው የካቲት 13 ቀን 1929 ዓ.ም ከጠላት ጦር በተተኮሰ ጥይት ተመትተው ወደቁ።



ሻቃ በቀለ የደጃዝማች ገብረማርያም ሞት ክፉኛ ቢያስደነግጣቸውና ቢያሳዝናቸውም ጦሩን የመምራት ኃላፊነታቸውን ተቀብለው ፍልሚያውን ቀጠሉ። በየካቲት ወር 1930 ዓ.ም በሶዶና በሜጫ ወሰን ላይ ሁለት ባታልዮን የጠላት ጦር ገጥመው ድል በማድረግ ጀግንነታቸውንና ጥንካሬያቸውን አስመስክረዋል። በዚሁ ወር ተከታታይ ጦርነቶችን ያካሄዱ ሲሆን በተለይም አገምጃ ላይ ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ ቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በአውሮፕላንና በመድፍ ከታገዘው የወራሪው ጦር ጋር ያደሩጉት ፍልሚያ የሚዘነጋ አይደለም። በዚህ ውጊያ ላይ ብዙ አርበኞች ቢረግፉባቸውም የማታ ማታ ድሉ የእርሳቸው ሆኗል። የጀግናውም ሻቃ በቀለ የጀብዱ ሥራ ከቀን ወደ ቀን እያደገና እየጎላ በመምጣቱ የሀገር ነጻነት የጠማው ጀግና ሁሉ ከጦራቸው ጋር ተሰልፎ መስዋዕትነት ለመክፈል ወደ እርሳቸው መጉረፍ ጀመረ።

በግንቦት ወር 1932 ዓ.ም የፋሺስት ጦር 24ኛ ብርጌድ አዛዥና የሶዶና ወሊሶ አካባቢ ገዢ ሆኖ የተሾመው ኮሎኔል ካዛባሳ ጦሩን ይዞ ከአዲስ አበባ ወደ ጎጌቲ ሲያልፍ የሻቃ በቀለ ወያ ጦር መንገድ ላይ ጠብቆ በመውጋት ለወሬ ነጋሪ እንኳ ሳያስተርፍ ደመሰሳቸው።

ቀኛዝማች ታደሰ ዘወልዴ ስለክስተቱ ሲገልፁ ‹‹ ... በ18 ካሚዮን የነበሩትን ፋሽስቶች አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጨረሷቸው። ወዲያውኑ አስከሬናቸው በፍጥነት ወደነበሩበት ካሚዮን እንዲሰበሰብ ከተደረገ በኋላ ናፍጣ አርከፍክፈውና በእሳት አቀጣጥለው ሌሊቱን እንደጧፍ ሲነድ አደሩ ... ›› በማለት ጽፈዋል።

የሻቃ በቀለ ጦር የጠላትን ጦር ድል እየመታ ስለቀጠለ የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ሻቃ በቀለ በነበሩበት አካባቢ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ለወራት ያህል ለማቋረጥ ተገዶ ነበር። ከደጃዝማች ገብረማርያም ሞት በኋላ ሻቃ በቀለ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን አርበኞች ጋር ኅብረት ፈጥረው ጠላትን በጋራ ተፋልመዋል። ለአብነት ያህል ከራስ አበበ አረጋይ እና ከደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ጋር የፈጠሩት ወዳጅነትና ኅብረት ተጠቃሽ ነበር። የፋሺስት ጦርም ሻቃ በቀለና ጦራቸው ከፍተኛ መስዋዕትነት እንዲከፍሉ ያደረጋቸውን የበቀል ርምጃ ወስዶባቸዋል። ይሁን እንጂ ይህ የበቀል ርምጃ ሻቃ በቀለን ከነፃነት ተጋድሏቸው ሊያሰናክላቸው አልቻለም።

በመጨረሻም ወራሪው የፋሺስት ጦር በሻቃ በቀለና በሌሎች ኢትዮጵያውያን አርበኞች እልህ አስጨራሽ ትግል ከኢትዮጵያ ምድር ተባረረ። ንጉሠ ነገሥቱ ከስደት ከተመለሱ በኋላ ሻቃ በቀለ የደጃዝማችነት ማዕረግ ተሰጣቸው። ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ሀገረ ገዢ በመሆን ተሹመው አገልግለዋል። የክብረ መንግሥት የወርቅ ማዕድን ኃላፊና የሁለተኛ ሬዥማን አዛዥ ሆነውም አገልግለዋል። ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ታሪካዊ መዝገበ ሰብ›› በተባለው መጽሐፋቸው በ1936 ዓ.ም ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ከጎጃም ተይዘው መጥተው እስር በተፈረደባቸው ጊዜ ወደ አዲስ አበባ እስኪዛወሩ ድረስ ለተወሰኑ ወራት የቆዩት በደጃዝማች በቀለ እጅ እንደነበር ጠቅሰዋል።

ለሀገራቸው ነፃነት በዋጋ የማይተመን አስተዋጽኦ ያበረከቱትና በቅንነት ሲያገለግሉ የነበሩት ደጃዝማች በቀለ ወያ፣ ባጋጣማቸው ሕመም ምክንያት በሀገር ውስጥ ሲታከሙ ቢቆዩም ስላልተሻላቸው ወደ ስዊዘርላንድ ሄደው ሊታከሙ በጉዞ ላይ ሳሉ ሚያዝያ 6 ቀን 1946 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። አስከሬናቸውም ሚያዚያ 10 ቀን 1946 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ሥርዓተ ቀብራቸው የመንግሥት ሹማምትንና የአርበኞች ማኅበር አባላትን ጨምሮ በርካታ ሕዝብ በተገኘበት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ተፈፅሟል። በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ወቅት ሕዝቡ የሻቃ በቀለ ወያን ጀግንነት ለመግለጽ እንዲህ በማለት ገጥሞ ነበር።

**‹‹አሳስኬድም አለኝ ጣልያን በመንገዱ፣**
**ያ ሻቃ በቀለ ና ወንዱ ና ወንዱ!››**

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

# ጭብጨባ የጠራት ብጽአት

ቤዛ እሸቱ

ጥሎባት ዘፈን ትወዳለች፤ የልቧን መሻት እንዳታጣጥም ቤታቸው ሙዚቃ የምትሰማበት ቴፕ ይሉት የለም። ‹‹ሳይደግስ አይጣላም›› ሆነና ጨርቆስ ከሚገኘው ቤታቸው ፊት ለፊት በ ‹‹ራህመቶ›› ሻይ ቤት ከጠዋት አንስቶ ሙዚቃ ይከፍታል። እሷም ነግቶ ሙዚቃ እስኪከፈትና መሽቶ እስኪዘጋ በጉጉት ትጠብቃለች። በሻይ ቤቱ ሸክላ ማጫወቻ የሚከፈቱትን ዘፈኖች አሳምራ ታውቃቸዋለችና ሁሌም አብራ ታዜማለች።

ብጽአት የዘፈን ፍቅር አድሮባታል። እናቷ ደግሞ ሙዚቃ የሚባል ነገር እንዲነሳ አይፈቅዱም። አጋጣሚ ሆኖ የመጀመሪያ ደረጃን የተማረችበት ፈለገ ዮርዳኖስና የሽመልስ ሀብቴ ትምህርት ቤት ከመደበኛ ትምህርት ሌላ የሙዚቃ ክበባት አልነበራቸውም።

በወቅቱ በየቀበሌው በግድ ይሰጥ የነበረውን ‹‹ንቃት›› የተሰኘ የወጣቶች የፖለቲካ ትምህርት ዕንቅልፍ እያዳፋት ትከታተል ነበር። በዚህ መሀል ከሌላ ክፍል የሚሰማው ተደጋጋሚ ጭብጨባ ያስገርማታል። በክፍለ ጊዜው እንድትነቃ ታስቦ የሚሰጣት የነማርክስና ሌኒን ትምህርት ጭራሽ እንቅልፍ ላይ እየጣላት ተቸገረች። ይህ ሲታወቅ ሁሌም አዳራሽና መጸዳጃ ቤት እንድታጸዳ ቅጣት ይበየንባት ጀመር።

አንድ ቀን በዕንቅልፍ ከምትፈተንበት የፖለቲካ ትምህርት ክፍል እንዳለች ከውጭ ስለሚሰማው ተደጋጋሚ ጭብጨባ ጠየቀች። ኪነቶች መሆናቸው ተነገራት። ብጽአት ስለ ኪነት አንዳች አታውቅም። ምንድነው? ስትል ጠየቀች። ምላሽ አላጣችም። ከፖለቲካ ትምህርቱ ውጭ የኪነት አባል መሆን እንደምትችል ተነገራት።

ብጽአት የኪነት ቡድኑን ከተቀላቀለች ፖለቲካውን መከታተል እንደማይጠበቅባት ተረዳች። ‹‹በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ›› እንዲሉ በተማረከችበት ጭብጨባ ሰበብ በዕንቅልፍ ጥሎ የሚያስቀጣትን የፖለቲካ ትምህርት ተገላገለች። ፈጥናም የኪነት ቡድኑን ለመቀላቀል ወሰነች።

የኪነት አባል ከሆኑት የሰፈር ጓደኞቿ አብዲ ኡመር አንዱ ነበር። አብዲን እንዲያስገባትና ማጨብጨብ እንድትችል ለመነችው። በጨዋታ፣ በቀልድና ድብድብ ለምትታወቀው ብጽአት ምላሹ ጥሩ አልሆነም። ስለምትረብሽ እንደማይሆን ነገራት። ጸባይዋን ለማረም ቃል ገብታ የቀበሌያቸውን ኪነት ተቀላቀለች።

ይህ የጨዋታ አዋቂዋ ድምጻዊት ብጽአት ሥዩም የሙዚቃ አጀማመር ነው። ወቅቱ የአብዮት ጊዜ ነበር። በቀበሌያቸው ኪነት የሚዘመሩ ሀገርን የሚያወድሱ ዘፈኖችን በጭብጨባ ማጀብና መቀበል ተግታ ትለማመድ ያዘች።

በጭብጨባ የማጀብ ሥራዋን ወዳዋለች፤ ከዛ እንቅልፏን ከሚያመጣባት ንቃት የፖለቲካ ትምህርት አድኗታል። አሁን የሌኒና የማርክስ ታሪክና የፖለቲካ ውሳኔ የለም። ስለዚህ በማጨብጨብ ማጀቡንና መቀበሉን ትለማመዳለች። የቀበሌው የኪነት አባላት ዝግጅታቸውን ለቀበሌው ነዋሪ ሊያቀርቡ ሁሉ ሙሉ ሁሉ ዝግጁ ሆኗል። የድግሱ ታዳሚ በስፍራው ተገኝቷል። ዋና ድምጻዊቷን በጭብጨባና በድምጽ የሚያጅቡ በተጠንቀቅ ላይ ናቸው። በድንገት ግን አንድ ጉዳይ ተሰማ። የዋናዋ ድምጻዊት እናት ድንገት መታመም ቡድኑን አጉድሎታል። ድምጻዊቷ ሁሉን ትታ ወደ ሆስፒታል ገሰገሰች።

የአስተባባሪውን መጨነቅ ያስተዋለችው ብጽአት ‹‹ምን ሆንክ?›› ስትል ጠየቀች። ‹‹ልጅቷ ቀረችብኝ ጉድ ሆንኩ›› አላት። ለዚህ ነው እንዴ እኔ እዘፍንልሃለሁ አለችው። የሰማውን አላመነም ‹‹ከመጣሽ ሳምንትሽ ነው። ዘፈኑን አታውቂውም›› ሲል ሞገታት። ምላሿዋ አልተቀየረም። ደጋግማ ‹‹አውቀዋለሁ›› ስትል አረጋገጠችለት።

ከዚህ ቀደም ለብቻዋ ስትዘፍን ሰምቷት አያውቅምና ወደጓሮ ወስዶ ‹‹እስቲ ዝፈኚልኝ›› አላት። ግጥምና ዜማውን ይዛው ኖሮ አሳምራ ተጫወተችው። በድምጿ ውበት የተማረከው አስተባባሪ እንደውም ልጅቷ ብትመጣም አንቺ ነሽ የምታቀርቢው አላት። በዚህ መልኩ የቀበሌው ኪነት ዋነኛ ድምጻዊት ሆነች።

በቀበሌ አንድ ተብሎ የጀመረ የብጽአት ድምጻዊነት ወደ ከፍተኛ ኪነት አደገ። የተለያዩ ዝግጅቶች ሲኖሩ አድማቂ ሆነች። በአካባቢው የካድሬ ሠርግ ሲኖር ያለብጽአት የማይታሰብ ሆነ። እንደተለመደው አንድ ቀን ሠርግ እንድታጅብ ተነገራት። እናቷ ለጉዳይ ከቤት ሊወጡ ሲሰናዱ ቤት እንድትጠብቅና ታናናሾቿን እንድትንከባከብ ያዟታል። ‹‹ሠርግ አለብኝ›› ብትልም ዛሬ አርፈሽ ቁጭ በይ ከቤት እንዳትወጪ ትእዛዛቸው ሆነ።

ብትጠበቅ ብጽአትን የበላ ጅብ አልጮህ አለ፤ እንደምንም ከቤት ወጥታ እናቴ ስለከለከለችኝ አልመጣም አለቻቸው። ምን ሲደረግ በአብዮት ጊዜ ይህ ይሞከራል። እናቷ ወደ ቀበሌ፣ እሷን ወደ ሠርጉ ወሰዱ። ብጽአት ሠርጉን፣ መልሱንና ቅልቅሉን ያለተቆጪ አጀበች። ከድግሱ መጠናቀቅ በኋላ በብጽአት ልመና ከእስር የተፈቱት እናት ልጃቸውን ለመከልከል አልሞከሩም። መዘዙን አይተዋልና ዝግጅት ባላት ጊዜ ለመላክ ፈቃጅ ሆኑ።

በየቦታው ተፈላጊነቷ የጨመረው ብጽአት የ17 ዓመት ወጣት ሳለች የልጅ እናት ሆነች። መጀመሪያውኑ ከእጅ ወደአፍ በሆነው ኑሮ ላይ የልጅ እናት መሆኗ ቤተሰቡን አስከፋ፤ እሷም ከኪነቱ ራቀች። ልጇ ሁለት ዓመት ሲሞላው ምን ሰርቼ ቤተሰቤን ልደግፍ? ልጄንስ ላሳድግ? ብላ ማሰብ ጀመረች። አንድ ጓደኛዋ አዝማሪ ቤት እንድትሰራ ሀሳብ አቀረበላት። ምንድነው አዝማሪ ቤት ስትል ጠየቀች ‹‹ቋራ›› ምግብ ቤት ይዟት ሄደ። ማታ የሚሰራ መሆኑን ስታውቅ እናቷ እንደማይፈቅዱ አውቃ ስጋት ገባት። እናት ሲሰሙ ምን ሲደረግ አሉ። እናቷ በማታ ቡና ቤት ለሚያስመሽ ሥራ ይሁንታ አልሰጡም። ሥራውን ሄድ መለስ እያለች ሞከረችው። ደሞዝ ባይኖረውም በሽልማት ደህና ገንዘብ ይገኝበታል። የእናቷ ቁጣ በረታ። ለትንሽ ጊዜ ከቤት ወጥታ ከሴት ጓደኛዋ ቤት መኖር ጀመረች።

በቋሚነት ቋራ ምግብ ቤት በአዝማሪነት መሥራት ጀመረች። ሆኖም እሷ የምታውቀው ዘፈንና የአብዮት መዝሙር ከአዝማሪ ቤት አልገጥም ቢላት ተቸገረች። እሷ የምታውቃቸውን ዘመናዊ ዘፋኞች እየጠራች ለባለ ማሲንቆ እንዲያጅባት ብትጠይቅ የማይሆን ሆነ።

የድምጿን ውበት የተመለከቱ በቤቱ የነበሩ የሙዚቃ ባለሙያ የባህል ዘፈን እንድታጠና መከሯት። ለማጥናት ዘፈኑን ማግኘት ያስፈልጋልና ግራ ገባት። ያኔ የመጣላት በኢትዮጵያ ሬዲዮ የዘፈን ፕሮግራም ያቀርብ የነበረው ጋዜጠኛ ታምራት አሰፋ ነበር። ባታውቀውም እሱን ፍለጋ ቢሮው ድረስ ሄደች። ጀማሪ ዘፋኝ መሆኗን ነግራ ለጥናቷ የሚያግዙ ዘፈኖችን በቴፕ ቀድቶ እንዲሰጣት ጠየቀችው። ቴፕ ከሌለሽ በምን ትሰሚዋለሽ አላት። የጓደኞቿን ቤት ቴፕ ጠቆመችው። ‹‹ባለውለታዬ›› የምትለው ጋዜጠኛ የተለያዩ ሙዚቃዎችን ከሪል በካሴት ቀድቶ ሰጣት።

የተለያዩ የባህል ዘፈኖችን ከመስማት ባለፈ ተለማመደች። አዝማሪ ቤት የሚፈልገውን ታዳሚውን በግጥም ማወደስ ከሌሎቹ እያየች በሂደት ተማረች። በሽልማት 80 ብር ያገኘች ቀን የያዘችው መንገድ ልክ መሆኑ ገባት። ሥራውን ደጋገመችው።

ብጽአት ሽልማቷን አጠራቀመች። 390 ብር በእጇ ቆጠረች። እሱን ይዛ እናቷ ቤት ገባች። እናቷ የብሩ ብዛት ቢገርማቸው የልጃቸውን የድምጽ ኃይል መረዳት ጀመሩ። ያኔ ወደ እናቷ ቤት ተመለሰች። ሙዚቃ ሰምታ የምትለማመድበት ቴፕ ቢኖራቸው ጥሩ ድምጻዊት እንደምትሆን አሳመነቻቸው ቴፑን ገዙላት።

ብጽአት ራስ ቲያትር ማስታወቂያ ማውጣቱን ተከትሎ ልትቀጠር ሄደች። ፈታኞቹ ‹‹ዝፈኚ›› ሲሏት የመሀሙድን የፍቅር ወጥመድ ነው አቀነቀነች። ‹‹የሴት ዘፈን ቀይሪ›› ተባለች። ጭቅጭቁ ቀርቶ አሃሃሃ እያለች የመሀሙድን ደገመች። ‹‹ኧረ! የሴት›› አሏት። የጥላሁን ገሰሰ ምግብማ ሞልቷል ... እኔን ያከሳኝ የፍቅር ርሃብ ነውን አዜመች። ‹‹ ኧረ! የሴት ሲሉ ዳግም ጮሁባት። እንባዋን እየዘረገፈች እኔ ይሄን ነው የማቀው አለች። ወዲያው ግን ‹‹ድንገት ሳላስበው፣

**ውጥን ሳይኖረኝ፣**

**የሚያስለቅስ ፍቅር በድንገት ያዘኝ።**

**ብሳ ከለቅሶዋ ተመለሰች።** ወዲያው አንደኛ ወጥታ ማለፏን ሰማች። ደሞዙም የተወዛዋዥ መሆኑ ተነገራት። በአዝማሪ ቤት በሽልማት ለምትንበሻበሸው ብጽአት ደሞዝ የተባለው 90 ብር ከትራንስፖርትና ከአንዳንድ ወጪዎች አያልፍም። አላዋጣ ቢላት የአዝማሪ ቤት ሥራዋን ቀጠለች።

ከቋራ ቀጥሎ ባምቢስ ይገኝ የነበረው የወይዘሮ እልፍነሽ ቤት መሥራት ጀመረች። በቤቱ ያለ ደመወዝ በሽልማት ብቻ መሥራት ያዘች። ስፍራው ታዋቂ ሆነ። ‹‹የብጽአት ቤት የሚል ሥያሜም ተቸረው።›› ቀስ በቀስ ዝናዋ እየጨመረ በመሄዱ ብጽአት ቤት እንሂድ እያሉ የሚሰበሰቡበት የበርካቶች መቃጠሪያ ሆነ። በስፍራው ሳለች የአምባሰል ሙዚቃ ቤት ባለቤት ፍቃዱ ዋሪና፣ የዜማ ደራሲው አበበ መለሰ ተገኝተው ብቃቷን በአካል አረጋገጡ።

ባይዋት ቀን ‹‹ካሴት እንሰራልሻለንና ነገ ልምምድ ጀምሪ›› አሏት። በወቅቱ በሙዚቃ ቤቱ የሰለሞን ተካልኝን አልበም ጀምረው ነበርና አንድ ለብቻዋና ሁለት ዘፈኖችን ከሱ ጋር በቅብብል የሰሩበት የመጀመሪያ የጋራ አልበም ‹‹ፋጡማ›› በሚል ርዕስ ወጣ።

አልበሙ እንደወጣ ወዲያው አምላክ ተረዳ ሙዚቃ ቤት ሌላ አልበም የመሥራት እድል አመቻቸላት። ብጽአት ሥዩም ከፀሐይ እንዳለ፣ ወረታው ውበትና ከተማ መኮንን ጋር 4 ድምጻዊያን በአንድ ሲሉ በጋራ የሰሩት አልበም በገበያ ዋለ። ከሰለሞን ተካልኝ ጋር ካወጡት አልበም በጋራ የዘፈኑት አንድ ዘፈን ተቀርጾም በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን የመታየት እድል አገኘች። ዝናዋ፣ ተፈላጊነቷም ሆነ ብቃቷ ይበልጥ እየጨመረ ሄደ። ከዛ በኋላ የተለያዩ ቤቶች ስትሰራ ቆይታለች። በመጨረሻም የራሷን ትክክለኛ የብጽአት ቤት ከፍታ ታዳሚውን አዝናንታለች። በሷ ቤት ነበር የብጽአትና የአበበ ፈቃደ ጥምረት የተፈጠረው።

እሱ ማሲንቆውን እየተጫወተና በድምጹ እየቀለጸ፣ ከእሷ ጋር በአንድ እየተቀባበሉ በግሩም ሁኔታ ታዳሚን አዝናንተዋል። ብጽአት ‹‹የአዝማሪን ቤት ሥራ ከፍ ያደረግንበት፣ ብዙ ዓለም ያየንበት ወርቃማ ጊዜያችን›› የምትለው ጥምረት ነበራቸው። ብጽአትና አበበ በማሲንቆአቸው ታጅበው የባህል ምልክት ተደርገው እስኪቆጠሩ ድረስ ያልተጫወቱበት ቦታ የለም። ከአበበ ጋር የነበራቸው ጥምረት የሚገርም ቢሆንም በ1991 ዓ.ም በወጣው አልበሟ ውስጥ የሚገኘው ‹‹አደራ ልጄ›› የተሰኘው ሥራዋ ከሁሉም ልቆ መታወቂያዋ ሆኖ ነበር።

አልበም ለመሥራት ከግጥም ደራሲ ሙሉጌታ ተስፋዬ ጋር ዝግጅት እያደረጉ ያለበት ወቅት የበኩር ልጇን ወንድሟ ዘንድ አሜሪካ ሰዳ በናፍቆቱ እየተብሰለሰለች ነበር። በየወሩ ከፍተኛ ወጪዋም የስልክ ክፍያ ሆኗል። እቤት ስትገባ በወንድሟ የተናደዱትን እናቷን ለምን አትተይውም የሚል ምክር ትለግሳለች። ወልደሽ የለም ይተው እንደሆነ እናያለን አሉት። ልክ እኮ ናት እናቴ ስትል ለግጥም ደራሲው አያ ሙሌ ታሪኩን ነግራ ግጥም እንዲጽፍላት ትጠይቀዋለች። በወቅቱ ደራሲው ከሁለት ልጆቹ ጋር ተለያይቶ ናፍቆት ላይ ነበር። በተመሳሳይ የዜማውም ደራሲ ሙሉጌታ አፈወርቅ ባለቤቱ ልጆቹን ይዛ ተለይታው ነበርና ሦስት የልጅ ብሶተኞች በጋራ ‹‹አደራ ልጄ››ን ፈጠሩ። ዘፈኑ የልጅ ፍቅርንና የእናትን ውለታ ሳይረዱ ቆይቶ ልክ እናት ሲሆን መረዳትንና እናትን ለበደሉት ጥፋት ይቅርታ መጠየቅን ያነሳል።

ይሄን ዘፈን ከሌሎቹ ዘፈኖቿ በተለየ እናቷ በሕይወት እያሉም ሆነ ካረፉ ወዲህ በእንባ ታጅባ ለቅሶዋ ሲበረታ በመሀል አቋርጣ የምትዘፍነው ዘፈኗ ነው። ብጽአት የትዳር ሕይወቷም የሰመረና በርካቶች የሚቀኑበት ነው። ሆኖም ከትዳር አጋሯ ተዋናይና አዘጋጅ ተስፋዬ ገብረሃና ጋር የተገናኙት ‹‹ባመንኩት ተከዳሁ›› ብላ ባሰበችበትና ‹‹ሰውን ማመን በቃኝ›› ብላ ብቸኝነትን በመረጠችበት ወቅት ነበር። አንድ ቀን ብሔራዊ ትያትር ተወዳጁን ተዋናይ ተስፋዬን አይታ የተሰማትን ስሜት አልወደደችውም። እናም ለፈጣሪዋ ጸለየች ፈጣሪ አሁንም ሰው ወድጄ ልጎዳ ነው ምን በደልኩህ ስትል ተማረረች።

ትውውቁ ፈጣሪ ተካሽበት ሲል ያዘጋጀላት ሆነና ሰዎች አጥንተው አስጠንተው የሚገቡበት ግንኙነት ቢከሽፍም ከአንድ ቀን የቲያትርና የራት ግብዣ መልስ በጋራ ተጠቃለሉ። ‹‹ይቻላል›› የተሰኘው ዘፈን ለሱ የተሰራ መሆኑን ትናገራለች።

ወደደችው አሉኝ ብወደው፣

ያንን ሸጋ ጉብል ብፈቅደው፣

..........ይቻላል! ይቻላል! ማፍቀርም ይቻላል

እያለች መጀመሪያ የወደደችው እሷ መሆኑን በግልጽ ትናገራለች። ከእሱ ፍቅር ተስፋዬ የተሰኘች ሴት ልጅ ወልደው 27 ዓመታትን በትዳር ዘልቀዋል። ‹‹ይቻላል›› የተካተተበት ‹‹የባስረሳኝ›› አልበም መጠሪያ የሆነው ሙዚቃ አሰራሩ ይለያል።

‹‹ቴዲ አፖ›› እያለች አፍ ባልፈታ አንደበቷ በቴዲ አፍሮ አድናቆት የተሰቃየችው ልጃቸውን ሊያገኝ ድምጻዊው ከቤታቸው ይገኛል። ከመኖሪያዋ ባገኘው ፒያኖም ‹‹ባስረሳኝ›› ሲል የዜማ መያዣ ግጥም ይደርሳል። ይልማ ገብረአብ አሟልቶ ግጥም የደረሰለት ባስረሳኝ በ1997 ዓ.ም የወጣው አልበሟ መጠሪያና ተወዳጅ ሥራዋ ሆኗል።

ከሀገር የወጣችው እንደተለመደው ለኢትዮጵያ ሚሊኒየም ሙዚቃዋን በአውስትራሊያ አቅርባ ለመመለስ ነበር። እዛው አውስትራሊያ እያለች ታመመች። የወሰዷት የኢትዮጵያ ኮሚኒቲዎች የመጀመሪያ ሕክምናዋን ወጪ ሸፈኑላት። ለቀጣዩ ግን ሕክምናሽ እንዲቀጥል ወረቀትሽን አስተካክይ የሚል ምክር ቸሯት። የጤና ነገር ነውና ‹‹እስቲ ልሞክረው›› ብላ ያመለከተችው ወረቀት በሦስት ሳምንት ተሰጣት። በስምንት ወሯ ቤተሰቦቿን ወሰደች።

በሰው ሀገር ኑሮ ተጀመረ። አዲስ አበባ ሬስቶራንትን ከፈቱ። ከባለቤቷ ጋር ምግብ አብሳይ፣ እቃ አጣቢ፣ አስተናጋጅ፣ ገገር፣ አስተዳዳሪ ብቻ ሁሉንም ሆነው ሰርተዋል። ምግብ ቤቱን ስትጀምር ሀሳቧ ቀን ምግብ ቤት፣ ማታ ደግሞ ሙዚቃ የሚሰራበት ለማድረግ ነበር።

በአውስትራሊያ ያለው ታዳሚ ቁጥር አነስተኛ መሆን ሙዚቃ የመሥራቱን ሀሳብ አስጣለ። በዚህ ጊዜ ሁለቴ በአሜሪካ ሙዚቃ ከማቅረቧና ዓመት ከአውስትራሊያ ቆይታ በኋላ በኢትዮጵያ መድረክ ላይ ከመሥራቷ ውጭ ከሙዚቃ ተራርቃ ቆይታለች። አሁን ግን ከ15 ዓመታት የአውስትራሊያ ቆይታ በኋላ ወደ ሀገሯ ተመልሳ ከናፈቃት የሀገሯ አድማጭ ጋር ተገናኝታለች።



ብጽአት ስዩም

# ዓለም አቀፍ



## የኒጀር ወታደራዊ አመራሮች የፈረንሳይ አምባሳደር ሀገሪቷን በ48 ሰዓታት ለቀው እንዲወጡ አዘዙ

በኒጀር በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን የተቆጣጠሩት ወታደራዊ አመራሮች የፈረንሳይ አምባሳደር ሀገሪቷን በ48 ሰዓታት ለቀው እንዲወጡ ትዕዛዝ አስተላለፉ። በኒጀር እና በቀድሞ ቅኝ ገዥዋ ፈረንሳይ መካከል ያለው ግንኙነት ከቀን ወደ ቀን እየሻከረ ባለበት ወቅት ነው ይህ የተሰማው።

ወታደራዊ አመራሩ የፈረንሳይ አምባሳደር ከኒጀር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር ለመገናኘት ለቀረበላቸው የእንገናኝ የግብዣ ጥሪ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑም ብሏል። ፈረንሳይ በበኩሏ "ሥልጣንን በኃይል የተቆጣጠሩ ግለሰቦች" እንዲህ ያለውን ማባረር ለማዘዝ "ሥልጣን የላቸውም" ብላለች።

ኒጀርን በአንድ ወቅት በቅኝ ግዛት ይዛት የነበረችው ፈረንሳይ በቅርቡ የተካሄደውን መፈንቅለ መንግሥት የምትቃወም ሲሆን በኃይል ከሥልጣን የተገረሰሱት ፕሬዚዳንት መሃመድ ባዙም ወደ ሥልጣን መመለስ አለባቸው ስትልም ትሰማለች።የፈረንሳይ አምባሳደር እንዲወጡ ትዕዛዙ የተላለፈው በወታደራዊ አመራሩ በተሾሙት የኒጀር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነው።

መፈንቅለ መንግሥቱንም ተከትሎ የፈረንሳይ ሰንደቅ ዓላማ በአደባባይ የተቃጠለበትን ጨምሮ ሌሎች ተቃውሞዎች ተሰምተዋል።ኒጀር የፈረንሳይ የጦር ሰፈር መቀመጫ ስትሆን፣ በዓለምም ሰባተኛ የዩራኒየም ማዕድን አምራች አገር ናት። የዩራኒየም ማዕድን ለኒውክሌር ኃይል በጣም አስፈላጊ ግብዓት ነው።ሩብ የሚሆነው ይህ የኒጀር ማዕድን ወደ አውሮፓ በተለይም ወደ ቀድሞዋ ቅኝ ገዢዋ ፈረንሳይ ይላካል።

የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር "በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን የያዙ ወታደሮች ይህንን ጥያቄ የማቅረብ ሥልጣኑ የላቸውም። አምባሳደሩ በሀገሪቱ እንዲቀመጡ የተደረጉት በሕጋዊ መንገድ በተመረጡ የኒጀር ባለሥልጣናት ብቻ ነው" የሚል ምላሽ ሰጥቷል።

የኒጀር መንፈንቅለ መንግሥት መሪ የሆኑት ጄኔራል አብዱራህማኔ ቺያኒ ሀገራቸውን በሦስት ዓመታት ውስጥ ወደ ሲቪል አገዛዝ ለመመለስ ቃል ገብተዋል። ጄኔራሉ ይህንን ያስታወቁት ከምዕራብ አፍሪካ የምጣኔ ሀብት ማኅበረሰብ ኢኮዋስ አሸማጋዮች ጋር በዋና ከተማዋ ኒያሚ ከተገናኙ በኋላ ነው። ኢኮዋስ ፕሬዚዳንት መሐመድ ወደ ስልጣን መመለስ ድርድር ካልተሳካ ወታደራዊ እርምጃ እንደሚወስድ መዛቱ ይታወሳል።

የወታደራዊ አመራሩ ኒጀር ጦርነት እንደማትፈልግ፤ ነገር ግን ከማንኛውም የውጭ ጣልቃ ገብነት ራሷን እንደምትከላከል ተናግረዋል። ጄኔራሉ በተጨማሪም ኢኮዋስ የባህር በር በሌላት እና ድሃ በሆነች ሀገር ላይ የጣለውን ማዕቀብ "ሕገወጥ እና ኢሰብዓዊ" ነው ሲሉም ማውገዛቸውን ጠቅሶ ቢቢሲ ዘግቧል።

## ሞዛምቢክ በጥብቅ ስትፈልገው የነበረውን አሸባሪ መግደሏን አስታወቀች



ሞዛምቢክ በጥብቅ ስትፈልገው የነበረው እና ከእስላማዊ መንግሥት (አይኤስ) ጋር ግንኙነት ያለው የጂሃዲስት ቡድን መሪን መግደሏን አስታወቀች። መሪው በሀገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል እየተዋጋ እንደነበር የተገለጸ ሲሆን፤ በመንግሥት ኃይሎች መገደሉም ተነግሯል። ቦኖማዴ ማቹዴ ኦማር ወይም ኢብን ኦማር በመባል የሚታወቀው መሪ ጦርነቱ ከተጀመረበት ከጎሮጎሳውያኑ 2017 ጀምሮ አማጺያኑን ይመራ እንደነበር የሀገሪቱ መከላከያ ሚኒስቴር አስታውቋል።

ከኦማር በተጨማሪም ሌሎች ሁለት ከፍተኛ አመራሮች መገደላቸውን የመከላከያ ሚኒስቴር መግለጫ አትቷል። የሀገሪቱ መንግሥት ገድያቸዋለሁ የሚላቸውን አመራሮች በተመለከተ በገለልተኛ ወገን የተረጋገጠ ነገር የለም። ከሁለት ዓመት በፊት የአሜሪካ መንግሥት ኦማርን አሸባሪ በሚል ፈርጃታል።

በሀገሪቱ በካቦ ዴልጋዶ ግዛት በተፈጸሙ ጥቃቶች እንዲሁም ፓልማ በተሰኘው ሆቴል ለበርካቶች ሞት ምክንያት የሆነውን ጥቃት ያቀነባበረው ኦማር እንደሆነም አሜሪካ አስታውቃለች። ከአንድ ወር በፊት የሞዛምቢክ ጦር ከሩዋንዳ እና ከደቡብ አፍሪካ በመጡ በመቶዎች በሚቆጠሩ ወታደሮች በመታገዝ በአማጺያኑ ላይ ከፍተኛ የጥቃት ዘመቻ መክፈቱን አስታውቆ ነበር።

ኦማር እና ሁለት ተባባሪዎቹ በሠራዊቱ እና የውጭ አጋሮች ጋር በተደረገ የጋራ ዘመቻ በማኮሚያ በሚገኝ ጫካ ውስጥ መገደላቸውንም ነው መንግሥት ያስታወቀው። የሞዛምቢክ ፕሬዚዳንት ፊሊፔ ኒዩሲ ግድያዎቹ የተከናወኑት ማክሰኞ መሆኑን አርብ ዕለት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ተናግረዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሰሜናዊ ሞዛምቢክ እየተከሰተ ያለው ጦርነት ከአንድ ሚሊዮን በላይ ነዋሪዎች ቀያቸውን ለቀው እንዲወጡ አስገድዷቸዋል ብሏል። በሀገሪቱ ባለው ጦርነት በተጨማሪም በብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚገመት የነዳጅ ፕሮጀክት እንዲቆም አስገድዷል።

በጋዝ እና ሩቢ በተሰኘው ማዕድን የበለጸገችው የካቦ ዴልጋዶ ግዛት የተፈጥሮ ሀብቷን መበዝበዝ የሚፈልጉ በርካታ ቡድኖች መስህብ ናት። በአካባቢዋም በርካታ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ማዕድን በመቆፈር ሥራም ተሰማርተዋል። ምንም እንኳን አካባቢዋ በተፈጥሮ ሀብቷ የታደለች ቢሆንም በርካታ ሞዛምቢካውያን ለከፍተኛ ድህነት የተጋለጡባት ሥፍራ ናት።

የአካባቢው ነዋሪዎች ከመሬት እና የሥራ ዕድል ከማጣት ጋር በተያያዘ የሚያነሷቸው ቅሬታዎች አማጺያኑ በርካታ ሰዎችን እንዲመለምሉ አስተዋጽኦ አድርጓል። ጦርነቱ እየተካሄደበት ባሉት አምስት ዓመታት ሰላማዊ ዜጎች ከመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች እና አማጺያን አሰቃቂ ጥቃቶች እንደደረሰባቸው የሙብት ተሟጋቾች መናገራቸውን የቢቢሲ ዘገባ አመልክቷል።


### የጨረታ ማስታወቂያ

### የጨረታ ቁጥር OACF, AMF/SNCB/04/2015

የኦሮሚያ ግብርና ህብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ኃ/የተ.አሰላ ብቅል ፋብሪካ ያገለገሉ የተለያዩ የመካኒካል፣ ኤሌክትሪካል፣ አውቶመካኒካል፣ የመለዋወጫና የስራ መሳሪያዎች፣ የተለያዩ ያገለገሉ ሞተሮች፤ ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶች፤ የመኪና ጎማዎች፤ ራድያተር፤ የጭነት አይሱዙ ሙሉ እስፖንዳ፤ የተጋቡ የቀለምና የፎስቶክሲን ቆርቆሮዎች ባሉበት ሁኔታ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል።

ስለሆነም በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎትና አቅም ያላቸው ተጫራቾች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

1. ተጫራቾች የ2015 ዓ.ም የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN No./ ተመዝጋቢ ስለመሆናቸው ሕጋዊ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ አሰላ /ቁሉምሳ/ በሚገኘው የፋብሪካው የገበያ ጥናትና ሽያጭ ቢሮ ቁጥር 051 በመቅረብ የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ/ እየከፈሉ ዘወትር በስራ ሰዓት፣ ከሰኞ እስከ ዓርብ፣

* ጠዋት ከ2:00-6-00 ሰዓት

* ከሰዓት ከ7:00-10:00 ሰዓት

ቅዳሜ፣ ጠዋት ከ2:00-6:00 ሰዓት በመቅረብ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ።

3. ተጫራቾች የጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ የጠቅላላውን ዕቃ ዋጋ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ) በባንክ በተመሰከረለት ሲ.ፒ.ኦ /C.P.O/ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ መስከረም 08/2016 ዓ.ም እስከ 8፡00 ሰዓት ድረስ በአየር ላይ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡
5. ያገለገሉ የተለያዩ ዕቃዎች የሚገዙበትን ዋጋ በታሸገ ኤንቨሎፕ ብቻ አሰላ /ቁሉምሳ/ በሚገኘው የፋብሪካው የገበያ ጥናትና ሽያጭ ቢሮ ቁጥር 051 ወይንም አዲስ አበባ በሚገኘው ዋና መስሪያ ቤት (ከጀርመን አደባባይ ወደ ሚካኤል አደባባይ በሚወስደው መንገድ ላይ አድማስ ኮሌጅ አጠገብ በሚገኘው ህንፃ ላይ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 10) ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው።
6. ጨረታው በዕለቱ መስከረም 08/2016 ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዕለቱ በ8፡30 ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት አሰላ /ቁሉምሳ/ በሚገኘው የፋብሪካው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ይከፈታል፡፡
7. የጨረታ ሳጥኑ ከታሸገ በኋላ የጨረታ ሰነዳቸውን የሚያቀርቡ ተጫራቾች ተቀባይነት አይኖራቸውም።
8. ፋብሪካው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ስተጨማሪ ማብራሪያ፡**

ስልክ ቁጥር፡ 022 331 52 66 ወይም 022 331 81 97 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል።

**የኦሮሚያ ግብርና ህብረት ሥራ ማህበራት**
**ፌዴሬሽን ኃ/የተ.አሰላ ብቅል ፋብሪካ**



### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ወ/ሮ ዮርዳኖስ ብሩ እና በፍ/ባለዕዳ አቶ ልመነው ፈለቀ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር/99158 በ10/08/2014 ዓ/ም እና በኮ/መ/ቁ/139454 በ17/10/2014 ዓ.ም በ7/02/2015 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት 1ኛ በቦሌ ክ/ከተማ በአሁኑ (ለሚ ኩራ) ክ/ከተማ ወረዳ 10 ልዩ ስሙ 49 አካባቢ የሚገኝ በካ/ቁ/ቦሌ 10/53/9/4/52187/00 በወ/ሮ ዮርዳኖስ ብሩ ስም የተመዘገበ የይዞታው ስፋት 500 ካ/ሜ የሆነ ቤት የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 22,017,200 (ሀያ ሁለት ሚሊዮን አስራ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ብር) ውዝፍ የሊዝ ዕዳ ብር 1,040,072 ያለበት ሲሆን ከሽያጩ ይቀነሳል ለቀሪ የሊዝ አመታት ክፍያን ብር 4,400,000 ገዥ ይከፍላል የትራዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ የይዞታው ደረጃ 3/1 መሆኑ ታውቆ ጥቅምት 9 ቀን 2016 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ 9፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ 2ኛ በቦሌ ክ/ከተማ በአሁኑ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ልዮ ስሙ ሳሚት አካባቢ የሚገኝ በካ/ቁ/ቦሌ 10/54/4/12/36432/43899/01 በወ/ሮ ትርሀስ ሀዱሽ ስም የተመዘገበ የይዞታው ስፋት 1200 ካ/ሜ የሆነ ቤት የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 55,860,000 (ሃምሳ አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ሺህ ብር) ውዝፍ የሊዝ ዕዳ ብር 1,878,459.95 ዕዳ አለበት ከሽያጩ ይቀነሳል በቀሪ የሊዝ ዓመታት ሊከፈል የሚጠበቀው ብር 6,542,592 ሲሆን ገዥ ይከፍላል የትራዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ጥቅምት በ9 ቀን 2016 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ9፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናት ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመወሰድ ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን መነሻ ግምት 1/4 ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አፈ/ዳ/ ስም CPO አሰርቶ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ አሰርቶ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ የፍ/አፈ/ዳይሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሐራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመጻፍ ባለፈ ስም የማዛወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍ/አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

# ስፖርት





# ትንሹ አረንጓዴ ጎርፍ በማራቶን!

**ብርሃን ፈይሳ**

ከ13 ወራት በኋላ ኢትዮጵያ በሴቶች ማራቶን ዳግም የዓለም ቻምፒዮን መሆኗን አረጋግጣለች። የኢትዮጵያ የማራቶን ክብረወሰን ባለቤት አማኔ በሪሶ በቻምፒዮናው ለኢትዮጵያ ሁለተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ስታስመዘግብ፣ የአምናዋ ቻምፒዮን ጎተይቶም ገብረስላሴ የብር ሜዳሊያ ባለቤት ሆናለች።

በትናንቱ ማለዳ ውድድር ረጅሙን የ42 ኪሎ ሜትር ፍልሚያ አራት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በአስደናቂ የቡድን ሥራ በመተጋገዝ ለተፎካካሪዎቻቸው ከባድ የነበረውን ሙቀት መቋቋም ችለዋል። የነበራቸው የቁጥር የበላይነትና የቡድን ሥራም ጠንካራ የሥነልቦና የበላይነት አላብሷቸው ነበር። ይህም የአረንጓዴውን ጎርፍ ታሪክ ለመስራት እድል ፈጥሮላቸው ነበር። ያምሆኖ በነበረው ከፍተኛ ሙቀት ሦስቱንም ሜዳሊያ ማሳካት አልቻሉም።

በማራቶን ከታዩ ድንቅ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል አንዷ የሆነችው አማኔ በሪሶ በአስደናቂ ብቃት 2:24:23 የሆነ ሰዓት አሸናፊ የሆነችው አማኔ፣ ዘንድሮ በተካሄደው የቦስተን ማራቶን ሁለተኛ ደረጃን ብትይዝም በቫሌንሲያ ማራቶን ያስመዘገበችው 2:14:58 ሰዓት ከዓለም የምንጊዜም የማራቶን ፈጣን ሰዓት ሦስተኛ ነው።

የአምናዋ ቻምፒዮን አትሌት ጎተይቶም ገብረስላሴ 2:24:34 በሆነ ሰዓት የብር ሜዳሊያውን የግሏ ማድረግ ችላለች። እአአ በ2021 የበርሊን ማራቶን አሸናፊ እንዲሁም በቶኪዮ ማራቶን ሦስተኛ ደረጃን በመያዝ ነበር ያጠናቀቀችው። ባለፈው ዓመት የኒውዮርክ ማራቶን በተመሳሳይ 3ኛ ደረጃን በመያዝ ነበር የፈፀመችው።



ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሴቶች ማራቶን ያሳዩት የቡድን ሥራ የወርቅና የብር ሜዳሊያ አሸናፊ አድርጓቸዋል፣

እኤአ 2015 ላይ በቤጂንግ ቻምፒዮና በማሬ ዲባባ የተመዘገበው የመጀመሪያው የማራቶን የወርቅ ሜዳሊያ ባለፈው በኦሪገን በጎተይቶም ገብረስላሴ መደገሙ ይታወሳል። ዛሬ ደግሞ በአትሌት አማኔ በሪሶ የወርቅ ሜዳሊያው ሰልሷል።

ለሁለት ሰዓታት ቡድኑን ከፊት በመምራት ፀሀይ ገመቹ ለድሉ ትልቅ ሚና ተጫውታለች። እሷ ትልቁን ሥራ ጨርሳ አቋርጣ ስትወጣም አሸናፊዋ አማኔ በሪሶና የአምናዋ ቻምፒዮን ጎተይቶም እንዲሁም ያለምዘርፍ የኋላው ውድድሩን ተቆጣጥረው ወደፊት ገፍተዋል። ውድድሩ ሊጠናቀቅ ጥቂት ሲቀረው ግን ያለምዘርፍ የነሐስ ሜዳሊያ ለማጥለቅ የቻለችውን ሁሉ ጥረት አድርጋ አልተሳካላትም። በዚህም 2:26:13 ሰአት 5ኛ ሆና አጠናቃለች።

ይህ በርቀቱ በታሪክ ለኢትዮጵያ ሦስተኛው ወርቅ ሲሆን፣ በሴቶች ወርቅና ብር ሲመዘገብም የመጀመሪያ ነው። የአምና ቻምፒዮኗ ጎተይቶም ዳግም ቻምፒዮን በመሆን የኤድና ኪፕላጋትን ታሪክ የመጋራት እድል ቢኖራትም የብር ሜዳሊያ ማጥለቋ በራሱ በተከታታይ ቻምፒዮናዎች ወርቅና ብር በማጥለቅ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት አድርጓታል። የብር ሜዳሊያው በራሱም በቻምፒዮናው ታሪክ ኢትዮጵያ በሴቶች ማራቶን ያስመዘገበችው የመጀመሪያ ነው።

ውድድሩ እጅግ ጥቂት እስኪቀረው ድረስ የታገለችው ያለምዘርፍ የነሐስ ሜዳሊያውን ብታጠልቅ ኖሮ ኢትዮጵያውያን እኤአ 2011 ዴጉ ላይ ኬንያውያን ከአንድ እስከ ሦስት በማጠናቀቅ የሠሩትን ታሪክ መጋራት ይችሉ ነበር። ያምሆኖ አሁን ያስመዘገቡት ውጤት ለአትሌቶቹም ለኢትዮጵያም እጅግ የደመቀ ወደፊት በታሪክ ሊረሳ የማይችል ነው። ሞሮኳዊቷ ፋጡማ ጋርዳዲ 3ኛ በመሆን ድሉ በአፍሪካውያን እንዲቀር አድርጋለች።

ምሽት ላይ በተካሄደው የሴቶች 5ሺ ሜትር ፍፃሜ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ለአሸናፊነት የታጩ ቢሆንም ሜዳሊያ ውስጥ መግባት ሳይችሉ ቀርተዋል። በታክቲክ ፍልሚያ በታጀበውና እስከመጨረሻዎቹ ሜትሮች ድረስ በርካታ አትሌቶች በአጀብ በተጓዙበት ውድድር ኬንያዊቷ አትሌት ፌዝ ኪፕየጎን በውድድሩ ሁለተኛ የወርቅ ሜዳሊያዋን ስታሸንፍ፣ ሆላንዳዊቷ ሲፈን ሀሰን ሁለተኛ እንዲሁም ሌላኛዋ ኬንያዊት ቢያትሪስ ቺቤት ሦስተኛ በመሆን የሜዳሊያ ሰገነት ላይ የሚያስወጣቸውን ድል አስመዝግበዋል።

በውድድሩ ላይ የተሳተፉት ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች እጅጋየሁ ታዬ አምስተኛ፣ መዲና ኢሳ ስድስተኛ፣ ፍሬወይኒ ኃይሉ ሰባተኛ እንዲሁም ጉዳፍ ጸጋይ 13ኛ ሆነው አጠናቀዋል።




# የእውቀት ዛፍ - የልጆች ትምህርታዊ ዝግጅት

**እዮሩስ ተስፋዬ**

ሠላም ልጆች እንዴት ናችሁ? አዲስ ዓመት ሊገባ ጥቂት ቀናት ብቻ ናቸው የቀሩት። እና ለአዲስ ዓመት ምን ለማድረግ አቀዳችሁ? በትምህርታችሁ ጥሩ ውጤት ያመጣችሁ የበለጠ ለመጠንከር፣ ደከም ያላችሁ ካላችሁ ደግሞ ለማሻሻል እንዳቀዳችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም። ልጆች እናንተን እውቀት ለማስጨበጥ የመገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ)፣ ለምሳሌ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ፣ ሬዲዮ እና ሌሎችም ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ ታውቃላችሁ አይደል? ከዚህ ቀደምስ "ትምህርት በሬዲዮ" ተብሎ የተለያዩ የትምህርት አይነቶች በሬዲዮ ይሰጡ እንደነበርስ ሰምታችሁ፣ ወይም ወላጆቻችሁ ነግረዋችሁ ያውቃል? "በሚገባ!" አላችሁ ልጆች? ጎበዞች። ስለዚህም መገናኛ ብዙኃን ከብዙ ሰዎች ጋር በተለያዩ አማራጮች ስለሚደርሱ እናንተን ጨምሮ ሌላውን ማኅበረሰብ ለማስተማር ትልቅ ኃላፊነት እና አቅም አላቸው።

ልጆች፣ አሁን አሁን ልብ ብላችሁ ካስተዋላችሁ ደግሞ ለእናንተ የሚሆኑ የተለያዩ የልጆች የቴሌቪዥን ዝግጅት እንደ አማራጭ እየቀረቡ ናቸው። ይህ በጣም መበረታታት ያለበት ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ ያሉት በቂ ናቸው ተብሎ ግን አይታመንም። ዛሬ ግን አንድ አዲስ ትምህርታዊ የቴሌቪዥን ዝግጅት እናስታውቃችኋለን።

ልጆችን ማዕከል አድርገው ከሚሰሩ ማዕከላት መካከል "ኑ ጭቃ እናቡካ የልጅነት ማዕከል" አንዱ ሲሆን፣ በማዕከሉ ልጆች እንዴት እንጀራ እንደሚጋገር፣ እንዴት ጥጥ መፍተል እንደሚቻል፣ ሥዕል እንዲስሉ፣ ጭቃ እያቦኩ የሸክላ ውጤቶችን እንዲሰሩ በማጫወት እና በማዝናናት ብዙ ነገሮችን እንዲማሩ ይደረጋል።


አሁን ደግሞ በምን መጣ መሰላችሁ? ሕፃናትና ልጆች በቀላሉ ትምህርት እንዲገባቸው እና ፊደሎችን በቀላሉ መጻፍ እንዲችሉ በተግባር የተደገፈ ትምህርታዊ ዝግጅት ለማቅረብ የቅድመ ዝግጅት ሥራውን ጨርሶ በአዲስ ዓመት ለእይታ እንደሚበቃ ተነግሯል። ትምህርታዊ ዝግጅቱም የሚቀርበው በካናል ፕላስ፣ በድክድክ የልጆች ቻናል ነው። ዝግጅቱ በሁሉት የሀገራችን ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ "የእውቀት ዛፍ" የተሰኘ ስያሜ ሲኖረው፣ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ደግሞ "ኦዳ ቦሩምሳ" የተሰኘ ትምህርታዊ ዝግጅት እንደሚቀርብ የዝግጅቱ ፕሮዲውሰር አቶ ዮሴፍ ወልደአማኑኤል ገልጸዋል።

ልጆች እውቀት የሚገበዩበት አዲስ የትምህርት ፕሮግራም ለማስጀመር በሚገባ ተዘጋጅተናል ያሉት አቶ ዮሴፍ፣ ከልጆች በተጨማሪም ወላጆች (ሁሉም ሰው) በሚገባ እንዲመለከተው አድርገው ማዘጋጀታቸውን፣ በዝግጅቱም ወላጆች፣ ተማሪዎችና መምህራን የተሳተፉበት መሆኑን ተናግረዋል።

ልጆች "የቄስ ትምህርት" ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እንደ አሁኑ የመንግሥትም ይሁን የግል ትምህርት ቤቶች ከመስፋፋታቸው በፊት፣ በዘመኑ የነበሩ ሕፃናት ቄስ ትምህርት ቤት ገብተው ሀ ሁ . . . እያሉ (ፊደል እየቆጠሩ) በዛፍ ጥላ ስር ሆነው፣ ከየኔታ (መምህር) እግር ሥር ቁጭ ብለው ይማሩ ነበር። ስለዚህም የቄስ ትምህርት እንዳይረሳ በማሰብ በእውቀት ዛፍ ትምህርታዊ ዝግጅት ላይ ልጆች ከዛፍ ጥላ ሥር ቁጭ ብለው ፊደሎችን እንዲማሩ ይደረጋል። ወላጆችም አስተማሪ ከመቅጠር ይልቅ ይህንን ትምህርታዊ ዝግጅት በማሳየት ልጆቻቸውን ለማስተማር እንደሚያግዛቸው አዘጋጆቹ ይገልጻሉ። አዝናኝ በሆነ መልኩ፣ ማለትም በሙዚቃ (መዝሙር) የተለያዩ እንስሳትን ይዞ በመቅረብ እና ዛፍ ላይ የተሰቀሉ ፊደሎችን በማውረድ ስያሜያቸውን፣ እንዲሁም እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው በቀላሉ እንዲማሩ እንደሚረዳቸው አቶ ዮሴፍ ገልጸዋል።

ዕድሜያቸው ከሦስት እስከ አስር ዓመት ላሉ ሕፃናት ታስቦ የተዘጋጀው "የእውቀት ዛፍ" ዘወትር ቅዳሜ እና እሁድ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ በካናል ፕላስ ድክድክ ቻናል የሚቀርብ ሲሆን፣ የአፋን ኦሮሞው "ኦዳ ቦሩምሳ" ትምርታዊ ዝግጅት ደግሞ በጦጼ ቻናል ዘወትር ቅዳሜ እና እሁድ በተመሳሳይ ሰዓት ከመስከረም 05 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ለዕይታ ይበቃል።

ስለዚህም ልጆች አጋጣሚው እና ሁኔታዎች አመቺ ከሆኑላችሁ እናንተን ሊያስተምሩ የሚችሉ፣ ብሎም እውቀት ልታገኙበት የምትችሉባቸውን ትምህርታዊ ቴሌቪዥን ዝግጅቶች ከመምረጥ እና ከመከታተል በተጨማሪ፣ አጋዥ መጻሕፍትን በማንበብ በትምህርታችሁ ጎበዝ እንድትሆኑ ይረዳችኋል። የእረፍት ጊዜያችሁንም ዘና ፈታ ብላችሁ እንድታሳልፉ ያደርጋችኋል።




የእውቀት ዛፍ ትምህርታዊ ዝግጅት አቅራቢ መምህርቷና ተማሪዎቿ፣